Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
SEEK WISDOM, ELEVATE YOUR INTELLECT AND SERVE HUMANITY !

## የሂዩማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ-ምረቃ መርሐግብር

# የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ትንተና

(በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ2015 ዓ.ም.፣ ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት)

በሙሉ ደርቤ

አማካሪ

ጌታሁን አማረ (ፕ/ር)

ነሐሴ፣2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሐግብር

# የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ትንተና

## (በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ2015 ዓ.ም. ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት)

አማካሪ

ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአመራኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍን ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ-ምረቃ መርሐግብር**

የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ትንተና

(በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ2015 ዓ.ም. ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል

በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት)

በሙሉ ደርቤ

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1. ፐ/ር ጌታሁን አማረ | ________________ | ________________ |
| 2. የውስጥ ፈታኝ ስም <u>ዶ/ር ዳዊት</u> ፍሬህይወት | ________________ | ________________ |
| 3. ውጭ ፈታኝ ስም <u>ዶ/ር በኀሰው የሽዋስ</u> | ________________ | ________________ |

## ምስጋና

በቅድሚያ መሰናክሎችን ሁሉ እያሻገረ ከዚህ ፍጻሜ ያደረሰኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር ዛሬም ዘወትርም የተመሰገነ ይሁን፤አሜን፡፡

እንዲሁም እድሉን አመቻችቶ ከፍጻሜ እንድደርስ ላደረገኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ያለመሰልቸት ከጅማሬ እስከፍጻሜ ልባዊ ክትትልና ሙያዊ ድጋፋቸውን ሳይነፍጉኝ ለፍጻሜ እንድደርስ ለደከሙ አማካሪዬና መምህሬ ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡

እንዲሁም ያለምንም ሀሳብ ሆኜ ትምህርቴን እንድከታተል በከባድ ጭንቀት ውስጥ ሆኖ ልጄን እየተንከባከበ ከዳር እንድደርስ ለተባበረኝ ውድ ባለቤቴ እሸቱ ሞላ እና የእናትን ናፍቆት ታግሳ እየጠበቀች መስዋእት ለከፈለች ተወዳጇ ልጄ መክሊት እሸቱ አመሰግናችኋለሁ፡፡

በመጨረሻም የገጠሙኝን ችግሮች ተቋቁሜ ከፍጻሜ እንድደርስ በሞራል ለደገፈችኝ “የዶርም” ጓደኛዬ አለሚቱ አየነው፣ ሙያዊ ድጋፍ ላደረገልኝ የስራ ባልደረባዬ ሲሳይ መኮንን እና የመማሪያ መጻህፍቱን ከማፈላለግ ጀምሮ የቁሳቁስ ድጋፍ ላደረገልኝ ወንድይፍራው አወቀ እና ለገጠመኝ ትልቅ ፈተና ላብቶኝ በመስጠት ለተባበረችኝ ክልል ፈንታቢል እንዲሁም መረጃ በመስጠት ትብብር ላደረጉልኝ መምህራን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት በ2015 ዓ.ም. በአማራ ክልል ስራ ላይ በዋሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና ነው። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች የአቀራረብ መርሆዎችን ተከትለው መቅረባቸውን፣ የሰዋሰው ይዘቶቹ የአደረጃጀት መርሆዎችን ተከትለው መቅረባቸውን መተንተን እና በመጻህፍቱ ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደቀረቡ መፈተሽ የሚሉት ናቸው። የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጮች የመማሪያ መጻኅፍቱ ናቸው። በተጨማሪም በቃለ-መጠይቅ መረጃውን ለማጠናከር ተሞክሯል። የተሰበሰበው መረጃ በአይነታዊ ወይም በገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትኗል። በዚህም መሰረት በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ፣ ከግልፅነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተመጣጣኝነትና ከተገቢነት አንጻር ትተንትኗል። እንዲሁም የሰዋሰው ይዘቶቹን አደረጃጀት፣ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነት፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አንጻር ያላቸው ገጽታ ምን እንደሚመስል ተፈትሷል። ይህን ለማሳካትም ጥናቱ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በክለሳ ድርሳናት ከቀረቡ ጽንሰሀሳቦች አንጻር እየታዩ የተተነተኑ ሲሆን፣ በናሙናነት ከተመረጡ መምህራን በቃለ-መጠይቅ በተገኙ ምላሾች ትንተናውን ለማጠናከር ተሞክሯል። በመሆኑም የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን አቀራረብ በሚመለከት መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ከግልጽነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተመጣጣኝነትና ከተገቢነት አንጻር ችግሮች እንዳሉ ከትንተናው  ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል። ከአደረጃጀት አንጻርም፣ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶ ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነት አንፃር ችግሮች ያሉ መሆኑ፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቶች ተመጣጣኝ ሆነው ያለመቅረብ /በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት በስፋት ሲገኝ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት የተዘጋጁ ስድስት ይዘቶች ብቻ ናቸው። በስምንተኛ ክፍል ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትበስፋት ሲገኝ ከአተቃላይ ወደ ዝርዝር የተደራጁ ሁለት ይዘቶች ብቻ/ ችግሮች እንዳሉ ለማየት ተሞክሯል። በመጨረሻመም በዚህ ጥናት ውስጥ በሰዋስ   ይዘቶች አደረጃጀት ላይ የታዩ ድክመቶችን ለማሻሻል ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች  ተጠቁመዋል። የመጀመሪያው በጥናትና ምርምር ውጤቶች የተጠቆሙ አስተያየቶችን ወስዶ በዝግጅት ወቅት ተግባር ላይ ማዋል፣ ሌላው መማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ በተቻለ መጠን የአቀራረብና የአደጃጀት መርሆዎችን ተከትለው ቢዘጋጁ የሚሉት ናቸው።*

# የይዘት ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ..... I
አጠቃሎ ..... II
የይዘት ማውጫ ..... III
የሰንጠረዥ ማውጫ ..... V
የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ ..... VI
ምዕራፍ አንድ
መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 4
1.3. የጥናቱ ዓላማ ..... 5
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 6
1.5. የጥናቱ ወሰን ..... 6
ምዕራፍ ሁለት
ክለሳ ድርሳናት ..... 8
2.1. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የምንነት ..... 8
2.2. የሰዋስው ምንነት ..... 10
2.3 የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ..... 11
2.4 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ..... 12
2.4.1. ግልጽነት ..... 12
2.4.2. ትክክለኛነት ..... 13
2.4.3. ተመጣጣኝነት ..... 13
2.4.4. ተገቢነት ..... 14
2.5. የይዘቶች አደረጃጀት ..... 14
2.5.1. ተከታታይነት ..... 15
2.5.2. ተለጣጣቂነት ..... 16
2.5.3. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ..... 17
2.5.4. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ..... 17
2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 18
ምዕራፍ ሶስት
የጥናቱ ዘዴ ..... 21
3.1. የጥናቱ ንድፍ ..... 21
3.1.1. የናሙና አወሳሰድ ..... 21
3.1.1.1. የመፃህፍት ናሙና አወሣሰድ ..... 21
3.1.1.2. የዞን እና የከተማ ናሙና አወሳሰድ ..... 22
3.1.1.3. የትምህርት ቤት ናሙና አወሳሰድ ..... 22


Comment [h1]:

3.1.1.4. የመምህራን ናሙና አወሳሰድ .......... 22
3.1.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች .......... 22
3.1.2.1. የሰነድ ፍተሻ .......... 22
3.1.2.2. የቃለ-መጠይቅ .......... 22
3.2. የመረጃ ትንተና ዘዴ /ስልት .......... 24
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና የውጤት መብራሪያ .......... 25
4.1. የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ቅኝት .......... 25
4.2. የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ .......... 27
4.2.1. ከግልጽነት አንጻር .......... 27
4.2.2. ከትክክለኛነት አንጻር .......... 32
4.2.3. ከተመጣጣኝነት /ሚዛናዊነት አንጻር .......... 34
4.2.4. ከተገቢነት አንጻር .......... 37
4.3. የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት .......... 38
4.3.1. ከተከታታይነት አንጻር .......... 38
4.3.2. ተለጣጣቂነት .......... 45
4.3.3 . ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት .......... 47
4.3.4 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት .......... 50
ምእራፍ አምስት
ማጠቃለያና አስተያየት .......... 54
5.1 ማጠቃለያ .......... 54
5.2. የመፍትሄ ሀሳብ .......... 55
ዋቢ ጽሁፎች .......... 57
አባሪዎች .......... 60

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሰንጠረዥ 3.1፡- ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን አጠቃላይ መረጃ...............................23

ሰንጠረዥ 4.1፡- የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ መረጃ ............Error! Bookmark not defined.

ሠንጠረዥ 4.2፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ .........................................................................Error! Bookmark not defined.

ሠንጠረዥ 4.3፡- በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መጻህፍት ውስጥ ተከታታይነት አግኝተው የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችና የድግግሞሽ መጠን ....................Error! Bookmark not defined.

## የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ

- ግልጽነት----------በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች ተማሪዎች ሊረዷቸው በሚችሉበት መንገድ መቅረብ
- ትክክለኛነት-------በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች ትክክልና እውነተኛ ሆነው መቅረብ
- ተገቢነት-------የሰዋስው ይዘቶች ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ ከባድ ሆነው አለመቅረብ
- ተመጣጣኝነት-------የቋንቋ ይዘቶች ሲቀርቡ ከታላሚው ቋንቋ ልዩልዩ የሰዋስው ክፍሎች ሚዛናዊ ሆኖ መቅረብ
- ተለጣጣቂነት--------በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች ተደጋግሞ መምጣት
- ተከታታይነት--------በአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል በዛው የክፍል ደረጃ የተለያዩ ምእራፎች ተደጋግመው መምጣት
- ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር---------ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ህግ በቅድሚያ ገለጻ የሚያቀርብ አደረጃጀት
- ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ---------ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ህግ በቅድሚያ ምሳሌ የሚያቀርብ አደረጃጀ

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ዘመናዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳብ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳቦች በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነዚህም ውጤታዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰ ሀሳብና ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ጽንሰሃሳብ ናቸው። ሁለቱ ጽንሰ ሀሳቦች የተለያየ ባህሪ ያላቸው፣ በተለያየ ዘመን በተናጠል የተሰራባቸውና የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የነበሩዋቸው ናቸው (Batston፣1994)።

ውጤታዊ የሰዋስው የማስተማር ጽንሰ ሀሳብ ብዙ ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም ጠንካራ ጎኖችም እንዳሉት የቅርብ ጊዜ ጥናቶች ያስገነዝባሉ። ይዘቶችን ለመምረጥና ለማደራጀት የስነልሳን ትወራዎችን እንጅ የተማሪውን ፍላጎት መሰረት አለማድረጉ፣ ለቅርጽ እንጂ ለፍች ትኩረት አለመስጠቱ፣ ድርጊታዊ የማስተማር ስልት አለመጠቀሙና በራስ የመማር እድልን ለተማሪ አለመፍቀዱ ከሚሰነዘሩት ነቀፌታዎች ውስጥ ዋናዋናዎቹ ናቸው። በአንጻሩ ግብአቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረቡ፣ ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደቡና የጽንሰሃሳብ ግንዛቤን ማስጨበጡ ጠቃሚ ጎኖቹ ናቸው (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Harmer፣1991)::

ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልትም የራሱ የሆኑ ዳካማ ጎኖች አሉት። ፍጹም እንከን የለሽ አይደለም። ለፍች እንጅ ለቅርጽ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ግብአቶችን መርጦና አደራጅቶ ለተማሪ አለማቅረቡ፣ ውስን አላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ ተማሪውን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ ደካማ ጎኖቹ ናቸው (Batston፣1994፤Leech1994 Nunan፣1988)::

ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ውጤት-ወሂደት የቋንቋ ስልተ-ትወራ ተቀባይነትን አግኝቶ በስፋት እየተሰራበት ነው (Tonkyn፣1994፤Batston፣1994)። ይህ ዘዴ ቀደም ባሉተ ዘመናት ሲሰራባቸው በነበሩት በውጤታዊና በሂደታዊ ስልተ-ትወራዎች ጠናካራ ጎኖች ላይ የተመሰረተ ነው። በውጤት-ወሂደት ስልተ ትወራ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ለቅርጽም ለፍችም ትኩረት

መስጠት አለበት። የስነ-ልሳን ትወራዎችንና የተማሪውን ፍላጎት መሰረት አድርጎ፣ ግብአቶችንና ክንዋኔዎችን መርጦና አደራጅቶ ለተማሪው ማቅረብ ይኖርበታል። የተለያዩ የመማር ስትራቴጅዎችን ለተማሪው ሊያቀርበ ይገባል። የትምህርቱ አቀራረብ በቅርጽ ላይ ከሚደረግ የጽንሰ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢ ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባና የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ ላይ መገደብ እንዳለበት ወይም የተወሰነ አላማን ይዞ መነሳት እንዳለበት ምሁራኑ ይገልጻሉ።

በመሆኑም አንድን ቋንቋ በአፍ መፍቻነትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማር ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ስነ-ልሳናዊ እውቀት ሊያዳብርለት የሚችል የሰዋስው ትምህርት ያስፈልገዋል። ይሁን እንጅ አፍ-ፈት እና ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው በሚማሩበት ዓላማ፣ ወደ ትምህርቱ ይዘውት በሚመጡት ሰዋስውና የገሀዱ አለም እውቀት አይነትና መጠን፣ በመሳሰሉት ተላውጦዎች ስለሚለያዩ የተለያየ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ስልት ያስፈልጋሉ (Batston፣1994፤Leech፣1994፤Ur፣1996)።

የቋንቋ ትምህርት ዓጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማጎልበት፣ የስነ-ጽሁፍና የስነ-ልሳን እውቀትን ማዳበር ነው(የኢ.ፌ.ድ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣2004የአስረኛ ክፍል የተማሪው መጽሀፍ)።ይህም የትምህርቱ ትኩረት በክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓት ላይም እንደሆነ ያስገነዝበናል። ስለዚህ ከተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ይቻል ዘንድ የመማሪያ መጻህፍት በውስጣቸው የክህሎት፣ የስነ-ልሳንና ስነ-ጽሁፍ ይዘትነት ያላቸውን የትምህርት ግብዓቶች በአግባቡ የያዙ፣ በወጉ የተደራጁና ብቃት ያላቸው የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ማሰናዳትና በግባቡ ማደራጀት ያስፈልጋል (Brown፣ 1994)።

ከገለጻው መረዳት የሚቻለው ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አንዱ የስነ-ልሳን እውቀትን ማዳበር በመሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን ከመቻል ባሻገር ስርዓት ባለው መንገድ በቋንቋ መገልገል ይችሉ ዘንድ በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከሚካተቱት የክሂልና የስነጽሁፍ ይዘቶች በአግባቡ የተደራጁና ብቃት ያላቸው ሁነው መዘጋጀት እንዳለባቸው ነው። ይህም ሰዋስው የቋንቋ ትምህርት የትኩረት አቅጣጫ አንድ መስክ መሆኑን ያስገነዝበናል።

እንደ Bygate, M. et al. (1994) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ዘርፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ስፍራ በተመለከተ ከአፍ መፍቻ ወይም ከውጭ ቋንቋ ትመህርት ጋር በተያያዘ መልኩ

Comment [h2]: et al.

በትምህርትነት መስጠት አለበት የለበትም በሚል ረገድ ብዙ ክርክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጅ የሰዋስው ትምህርት በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ አብይ ጉዳይ ሆኖ ከመገኘት ያገደው ነገር የለም፡፡

በተጨማሪም የቋንቋን ትምህርት በተመለከተ በእርግጠኝነት መናገር ከምንችልባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ እውቀት ያለውነው ባየ(1987):: ምክንያቱም ትምህርቱ የእውቀትና የክህሎት ዘርፎችን ማስጨበጥ አለበት፡፡ ሁለቱም አንድ ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው፡፡እነዚህ ችሎታዎች ከሌሉ ባአግባቡ በቋንቋ ለመጠቀም የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በተጨማሪም የስዋሰውን ትምህርት አስፈላጊነት በሚመለከት ቋንቋን በመግባቢያነት መጠቀም የሰው ልጅ መለያ ባህሪ ነው፡፡ የቋንቋን ስርዓት መረዳት ወይም ለመረዳት መጣር የቋንቋ ምሁራን መለያ ነው(ጌታሁን፣2011)፡፡

ከቀረቡት ሃሳቦች የምንረዳው የሰዋስው ትምህርት አንዱ የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ እንደሆነ ነው፡፡ እንዲሁም የቋንቋ ተጠቃሚ ለመሆን የክህሎት ትምህርት ብቻ በቂ እንዳልሆነና ሁለቱም እውቀቶች ከአንድ ከተማረ ሰው የሚጠበቁ እውቀቶች መሆናችው ነው፡፡

ይህን ግብም ለማሳካት የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘት በሚገባ መደራጀትና መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ የመጽሀፍ ዝግጅት በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት መገምገምና መሻሻል ይኖርበታል፡፡

በሰዋስው አደረጃጀትና አቀራረብ ርእስ ዙሪያ የተለያዩ አጥኝዎች ጥናት አድርገዋል፡፡ በግኝታቸውም ክፍተቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ባዩ ተሾመ(2004) "በደቡብ ክልል ከአምስኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል አጥንቷል፡፡

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) በበኩሉ "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ያቀረበው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ .

ሰሚራ አሊ (2010) "በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" .

ከጥናቶቹ በግኝታቸው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ አንጻር በ2013 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የስርዓተ-ትምህርት ለውጥ ተደርጓል፡፡ በለውጡም መሰረት በ2015 ዓ.ም በአማራ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት አቅራቢም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ከላይ በተተቀሱት ክልሎች በተደረጉ ጥናቶች የተጠቆሙ ክፍተቶች በዚህኛው ክልል ምን ይመስላል የሚለውን ለማረጋገጥ ጥናቱን አጥንታለች፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት በአነሳሽ ምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያው የስርዓተ ትምህርት ማሻሻያ በመደረጉ፣የተተኳሪ የክፍል ደረጃዎቹ መጻህፍት የተቀየሩና ጥናት አልተደረገባቸውም ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ ጥናት ቢደረግባቸውም እንኳ በተደጋጋሚ መፈተሽ እንዳለባቸው የመስኩምሁራን ይናገራሉ፡፡ በተለያዩ አጥኝዎች የሰዋስውይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ ዙሪያ ችግሮች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም አጥኝዋ በመማር ማስተማሩ ስራዋወቅት ባለው ምልከታ ከስምንተኛ ክፍል አልፈው ወደ ዘጠነኛ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶች ላይ የመገንዘብም ሆነ የመስራት አቅም ችግሮች እንዳሉባቸው ተገንዝባለች፡፡ በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ ተተኳሪ መጽሀፎቹ የአንደኛ ደረጃ የመጨረሻዎቹ እርከን እንደመሆናቸው መጠን የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ምን ይመስላል የሚለውን ለመፈተሽ ፍላጎት ያደረባት መሆኑ የሚሉት ርእሰ ጉዳዩን እንድትፈትሽ ካነሳሷት ምክንያቶች የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን የአጥኝዋ የአቅም ውስንነት ስለሚኖር እንጂ ተማሪዎች በክሂሎች ትምህርት ላይ ብቁ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሊታሰብ ይገባል፡፡

መማሪያ መጻህፍት አንድ ጊዜ ተዘጋጅተው ሁሉም ነገር አያበቃላቸውም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት እየተገመገሙ ማሻሻያ እንደሚያስፈልጋቸው ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ስለሆነም የሚገመገሙበትን ምክንያት ምሁራኑ የሚሉንን ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሚገመገሙባቸው በርካታ መክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡እንደ Dubin እና Olshatain(1986)፤Stern(1992) እና Cunningsworth (1995) ገለጻ የቋቋ መማሪያ መጻህፍት በጥንቃቄ የተመረጡና በወጉ የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ስነልሳናዊ፣ ስነትምህርታዊ እና ስነልቦናዊ ሀሰቦቸ መሰረት ማድረግ ያለባቸው መሆናቸውን በመጠቆም በዝግጅት ወቅትም ይሁን ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ  በተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸውና በሚገኙ ምላሾችም ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው ይገልጻሉ፡፡

Donogh እና Show (1995) በበኩላቸው ግምገማ የሚያስፈልገው ስራ ላይ ያሉ መጻህፍትን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለመለየት ሲሆን፣ አዲስ የሚዘጋጁትን ደግሞ ተገቢነታቸውን ለመረጋገጥ ነው ይላሉ፡፡

Grant (1998) እንዲሁ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የተካተቱባቸውን የመማሪያ መጻህፍት ትኩረት ሰጥቶ የመመርመርን ተገቢነት ሲያስረዱ በምክንያትነት ያቀረቡት ሀሳብ "ምንም አይነት ችግር የሌለባቸው የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን አዘጋጅቶ ማቅረብ አቻልምና ነው" የሚል ነው፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ የምንረዳው የመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት በአንድ ጊዜ ተከናውኖ የማይጠናቀቅና እንከን የለሽ ሆኖ መዘጋጀት እንደማይችል ነው፡፡ ስለሆነም በየጊዜው እየተገመገሙ ጠንካራ ጎናቸው የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትና ደካማ ጎናቸው ደግሞ የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት እንረዳለን፡፡

ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢ መማሪያ መጻህፍት የሚገመገሙበትን የሙህራኑን ሀሳብ ምክንያትበማድረግ በ2015ዓ.ም በአማራ ክልል እተተገበሩ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻህፍት ብዙ ጥናት አልተደረገባቸውም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ምን ጥንካሬና ድክመት አለበት የሚለውን መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ አጥኝዋ ይህን ርእስ እንድታጠና አነሳስቷታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2015 ዓ.ም በአማራ ክልል በስራ ላይ በዋሉት የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘትን አቀራራብና አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ ከዚህ ዋና ዓላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

- በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች የአቀራረብ መርሆዎችን ተከትለው መቅረባቸውን መፈተሽ፣
- በመማሪያ መጻህፍቱ የተካተቱ የሰውስው ይዘቶች ከሰዋስው ይዘት የአደረጃጀት መርሆዎች አንጻር የቀረቡ መሆኑን መተንተን፣
- በሰዋሰው ይዘት ረገድ በትግበራ ላይ ባሉት መጻሕፍት ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደቀረቡ መፈተሽ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን በየጊዜው መፈተሽ ጠቀሜታ እንዳለው የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ምክንያቱም በሁሉም መልኩ ፍጹም እንከን-የለሽ የሆነ መማሪያ መጻህፍት ማዘጋጀት አይቻልምና፡፡ ስለሆነም መማሪያ መጻህፍትን በስራ ላይ ከዋሉ በኂላ በቀጣይነት መገምገሙ ያሉ ችግሮችን በሂደት ለማሻሻልና ድክመታቸው እየተወገደ ጥንካሬያቸው እየጎላ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችል አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህም ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. በጥናቱ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሚያዘጋጁና የሚያሻሽሉ አካላት ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብዓቶችን ይጠቁማል፡፡
2. በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጃት በመፈተሽ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ቀጣይነት እንዲኖራቸውና ደካማ ጎኖቻቸው ደግሞ ለወደፊት እንዳይደገሙ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡
3. ወደፊት በዚህ መስክ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡እዲሁም ለሚያስተምሩ መምህራን ችግሮቹን አውቀው በመማር ማስተማሩ ስራ ወቅት እርምት እየሰጡ እንዲሰሩ ጥቆማ ይሰጣል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

በጥናቱ በ2015 ዓ.ም. በአማራ ክልል ስራ ላይ የዋሉ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ብቻ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ በመማሪያ መጻህፍቱ ከተካተቱ ይዘቶች ውስጥ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ብቻ በምእራፍ ሁለት ከቀረቡት የመተንተኛ መስፈርቶች አንጻር ተተንትኗል፤ ሌሎች የቋንቋ ይዘቶች የትናቱ ተተኳሪ አልሆኑም፡፡ እንዲሁም መማሪያ

መጻህፍቱ ከመርሀ ትምህርቱና ከመምህሩ መምሪያ ጋር ያላቸው ዝምድና አልተዳሰሰም፤ ከዚህ በፊት ከነበሩ መማሪያ መጻህፍት ጋር አያነጻጽርም ምክንያቱም የአጥኝዋ የአቅምና የጊዜ ውስንነት ስላለ ነው። ከመረጃ መሰብሰብ ከኳያ በአማራ ክልል በተፈጠረው ወቅታዊ ሁኔታ የተነሳ ከመጽሀፍ አዘጋጆች መረጃ ለመሰብሰብ አልተቻለም።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የምንነት

ለቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዝግጅት መነሻ የሚሆነው የቋንቋ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማ ነው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጻህፍቱ የተባለውን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በመርሀ ትምህርቱ ዝግጅትና አደረጃጀት ወቅት የተካተቱ ይዘቶችን የያዙ መተግበሪያ ሰነዶች መሆን ይገባቸዋል፡፡

Grant (1987) የመማሪያ መጻህፍትን ምንነት ሲገልጹ፣ አንድ ሰው ወደማያውቀው አካባቢ ተጉዞ ለመድረስ መረጃ ወይም መመሪያ የሚሆነው የጉዞ ካርታ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትም ተማሪውን ወደ ተፈላጊው ዓላማ ለማደረስ የሚያስችሉ አስተማማኝኝ መሳሪያዎ ወይም ለተማሪዎቹየሚያስፈልጉ የትምህርት ካርታዎች ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡ አክለውም፣ እነዚሁ የመማሪያ መጻህፍት የተደራጁ፣ የተመጠኑ፣ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለተማሪዎች የሚያቀርቡ መሆን እንደሚገባቸውና ይህንንም በማድረግ ሂደት የተማሪዎቹን አካባቢያዊና ዳራዊ እውቀት መያዝ እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ የምንረዳው የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ከየት ተነስተን ወዴት እንደምነደርስ አቅጣጫ ጠቋሚዎቻችንእንደሆኑ ሲሆን፣ሲዘጋጁም የተመጠኑ፣ የተማሪውን ቀደምት እውቀት፣ የአካባቢውን ሁኔታ፣እድሜና ፍላጎት ወዘተ. ታሳቢ በማድረግ የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ለማስፈጸም የሚዘጋጁ መሳሪያዎች እንደሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ ያስችላቸው ዘንድ በቋንቋ ትምህርት ፍልስፍና፣ፖሊሲና ዓላማ ላይ ተመስርተው እና የመርሃ ትምህርቱን ዝግጅት መሰረት አድርገው የሚሰናዱ ሠነዶች መሆናቸውን ነው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የመማር ማስተማሩን ሂደት በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው በባለሙያዎች ይታመናል፡፡ በተለይም እንደነ Richards እና Rodgers (1986) እና Sheldon (1987) አይነቶቹ የመስኩ ምሁራን ተገቢ የሆነ ጥንቃቄና ትኩረት ባልተለየው መንገድ የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጫወቱት ሚና የጎላ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በእነሱ እምነት የህብረተሰቡን የእድገት ደረጃ፣ ወግ እና ባህል፣ እምነት አስተሳሰብና ፍላጎት፣ እንዲሁም የትምህርት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት

የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለተማሪው፣ ለመምህራኑና ለአጠቃላይ የትምህርት ሂደቱ ስኬታማነት አስፈላጊነታቸው የማይካድ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን በክፍል ውስጥ የመጠቀሙን አስፈላጊነት ሲገልጹም፣ተማሪዎች በጽሁፍ መልክ የቀረቡ መልመጃዎችን፣ እውነታዎችን ለመረዳትና ለማጎልበት የሚያግዟቸው ሰነዶች ናቸው፡፡ ይህን አባባላቸውን በምክንያት ሲያስደግፉም በመምህር በቃል የሚተላለፍ ትምህርት ከሽምደዳ ስለማያልፍ ቶሎ ይረሳል፡፡ በጽሁፍ የሰፈረ ትምህርት ግን ለማንበብ አመች ነው፤ ማለትም በእውነታዎች ላይ ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤን ለማዳበርና ግላዊ ግምገማ በማድረግ አመለካከትን ለማስፋት ከቃል ይልቅ በጽሁፍ የቀረበ ትምህርት ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጻህፍት ተማሪው መማር የሚገባውን ይዘት በጊዜው እና በተገቢ የማስተማር ዘዴ፣ለመማር በሚያስችል መንገድ ስለሚያቀርቡለት ስነ ትምህርታዊ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ መምህራን የሚማሩ የተለያዩ ተማሪዎች በአንድ አይነት የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሀፍ ስለሚጠቀሙ ተመሳሳይ ትምህርት እንዲያገኙ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ለመምህራኑም ቢሆን ጊዜና ጉልበታቸውን በመቆጠብ ነገሮችን አቅደው ለማቅረብ ያግዟቸዋልና ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

Allwright (1981) ስለ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት እንደሚያስረዱት፣ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በራሳቸው እንዲማሩ የሚያስችሉ መመሪያዎች ናቸው፡፡ መጻህፍቱ ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች፣መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን አካተው ይይዛሉ፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናት ወይም ለማገዝ የሚዘጋጁ ሲሆን፣ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የመወሰን አቅም ያላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ከገለጻው፣ መማሪያ መፃህፍት ለተማሪዎች ተገቢ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን፣ መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን የያዙና የማስተማሪያ ዘዴዎችንም የመወሰን አቅም እንዳላቸው ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በራሳቸው እንዲማሩ የሚያስችሉና ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚጓዙ ስለሚመሩ መማር ማስተማሩን የሚያግዙ መሳሪያዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

## 2.2. የሰዋሰው ምንነት

ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት ነው፤ይሁን እንጅ ይህ ስርዓት መሰረት በሚያደርጋቸው ተዋቃሪዎች ረገድ የግንዛቤ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ብዙዎቹ ብያኔዎች ዓረፍተ-ነገርን መሰረት ያደረጉና ሰዋስው የቃላትን ቅንጅት ስርዓት የሚመለከት፣ በዓረተ-ነገር ደረጃ የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሰረት ያደረገ ቅደም ተከተላዊ አገባብ ነው (Brown፣1994፤ Ur፣1996)

ሰዋስው፣ ሲባል ቃላት ተገጣጥመው ትክክለኛ አረፍተነገር የሚመሰርቱበት መንገድ ነው፡፡ በአጠቃቀም ረገድ ሰዋስዋዊ የምንለው ነገር በአረፍተ ነገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባነሰ መልኩ የሚታየወ ነው ፡፡ ለምሳሌ፣ "ሁለት ሊትሮች ወተት ገዛሁ፡፡" ቢባል በአረፍተ ነገር ደረጃ ሰዋስዋዊ አይደለም፡፡ ሁለት የሚለው ቃል እስካለ ሊትር በብዙ ቁጥር መጽፍ አይኖርበትም፡፡ ከዚያም ባነሰ መልኩ "ሄጄ" በሚለው ቅርጽ መነገርና መጻፍ ሲገባው "ሄድጄ" ቢባል ሰዋሰዋዊ አይደለም (Ur፣1996) ፡፡

በሌላ መልኩ Cross (1991) ሰዋስው ግዙፍ የትምህርት መስክ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ አያይዘውም ሰዋሰውን በሁለት ገጽታ ማየት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ገጽታዎች መዋቅር እና ሰዋስው በመባል ይታወቃሉ፡የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ አንዱ ሲነሳ ሌላውን ማንሳት ወይም ማሰብ አይቀሬ ነው፡፡ ለምሳሌ "በሬ ጥጃ ወለደ" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የቃላት አሰላለፍ/አወቃር ችግር የለም፡፡ ነገር ግን ፍችው አያግባባንም ወይም ትክክል አይደለም፡፡ እንግዲህ ይህንን ነው ሰዋስዋዊ የምንለው በማለት ግልጽ ያደርጉታል፡ Cross እንደሚሉት የቃላት በስርአት መሰለፍ በምሁራንና ተመራማሪዎች በጎ ፈቃድና መልካም አመለካከት የሚመጣ ሳይሆን የቋንቋው ተናጋሪ በመደበኛነት ያስለመደውን ቅደምተከተል ወይም አሰላለፍና ፍች በመጠበቅ ላይ ተመሰረተ ነው፤ ይህም እንደየቋንቋው ይለያያል፡፡

ምሁራኑ ሰዋስው ማለት ስርአታዊ የቃላት አሰላለፍ/ መዋቅር እንደሆነና ከአረፍተ ነገር መዋቅር ባነሰ መልኩሊታይ እንደሚችል ያስገነዝቡናል፡፡ በተጨማሪም ሰዋስው የሚለው እሳቤ የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሰረት ያደረገ ቅደምተከተላዊ አገባብ/አሰላለፍ/ እና ፍች በመጠበቅ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

*በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል። አንደኛውፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ "እውቀት" የሚጠቁመውንና በሰው ልጅ አእምሮውስጥ ያለውን ችሎታ ነው። በዚህ ንድፈሀሳባዊ እይታ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሲያውቅናሲጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስውአእምሯዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል። ሁለተኛው የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ከስነድምጽ እስከ ስነሀረግ ያለውን ገለጻ የሚጠቁመውነው። ይህ ፍቺ ከመጀመሪያው ፍች ጠባብ ነው (ጌታሁን፣2011)።*

በዚህ ጥናት ውስጥም ስለሰዋስው የተሰጡ ብያኔዎችን በመያዝ በአማርኛ ሰዋስዋዊ ስርዓት መሰረት ሰዋስውን ለማስተማር በተተኳሪዎች መማሪያ መጻሐፍት ውስጥ የተካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃደች ተገምግሟል።

## 2.3. የሰዋስው ትምህርት ትኩረት

በቀደምት የቋንቋ ትምህርት ክንውኖች ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጽና ህግጋት በማረብ ተማሪዎች በደንብ እንዲያጠኗቸውና እንዲካኗቸው ማስቻል ነበር። ለዚህም በምሳሌነት ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን መጥቀስ ይቻላል። Stern (1993) እና Larsen-Freeman (1986) እንደሚገልጹት ሰዋስው-ወትርጉም ዘዴ የታላሚው ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት ማቅረብ ነበር። ለሰዋስዋዊ ቅርጾቹ አጠቃቀም እንብዛም አይጨነቅም። በክፍል ውስጥም ጥንታዊ የስነጽኁፍ ውጤቶች የሚርቡ ሲሆን በነሱ ተንተርሶ የቃላት ሽምደዳና ሰዋሰዋዊ ትንተና ይሰጣል። በዚህ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችና ህግጋት ብቻ ማስጠናት ነበር ማለት ይቻላል።

በዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ግን የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርጾችንና ህግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም። እንደ Larsen-Freeman (1986) እና Cnningsworth (1995) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት የቋንቋው ቅርጽ ወይም መዋቅር(ድምጾች፣ ምእለላዶች፣አገበብ)፣ፍች (ቃላዊፍች፣ሰዋስዋዊ ፍች) እና አጠቃቀም (ማህበራዊ አጠቃቀም፣ ስነልሳናዊ አጠቃቀም፣ቀደምት እውቀት) መሆን አለበት፡ ሰዋስዋዊ ቅርጽ አንድ የቋንቋ ክፍል እንዴት እንደተዋቀረ ያሳያል። ፍች ደግሞ የሰዋስዋዊ ቅርጹን ትርጉም ያስገነዝባል። አጠቃቀምን በተመለከተ ባጭሩ ይህ ነው ማለት አይቻልም። ሆኖም ቀለል ባለ አገላለጽ በቋንቋውና ቋንቋው ለአገልግሎት በሚውልበት አውድ መካከል ያለውን ግንኙነት

Comment [h3]: በሀግ
Comment [h4]:

ይመለከታል፡፡ አውድ ስንል ደግሞ ማህበራዊ አውደ፣ ስነልሳናዊ አውድ፣ የዲስኩር አውድ ወይም የቋንቋው ተጠቃሚ ቋንቋው በአገልግሎት ስላለበት አውድ ያለው ቀደምት እውቀት ሊሆን ይችላል፡፡

Harmer (1987) ቀደም ሲል የቀረቡትን ሃሳቦች በሚደግፍ መልኩ የሰዋስው ትኩረት በሰዋስው ቅርጾች ወይም በመዋቅሮች ላይ ብቻ መነጣጠር እንደሌለበት ይስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰዋሰዋዊ ቅርጽ ወይም መዋቅር የተለያዩ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላሉና፡፡ ስለዚህ በሰዋስው ትምህርት ወቅት የቀረቡ ሰዋስዋዊ ቅርጾች ወይም መዋቅሮች ከቋንቋው አጠቃቀም ወይም አገልግሎት ጋር መዛመድ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ ገለጻዎችን፣ ምሳሌዎችንና መልመጃዎችን ለተማሪዎች በማቅረብ ማለማመድ ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ አዲስ ሰዋስዋዊ ይዘትን ለተማሪዎች ስናቀርብ ቅርጽ ብቻ ሳይሆን አገልግሎትንም ልናስተምር እንደሚገባ፣ ፍች ብቻ ሳይሆን አጠቃቀሙንም ልናሳይ የሚገባ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ስንመለከት የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቅርጽ ወይም በመዋቅር ላይ ብቻ ያነጣጠረ መሆን እንደሌለበት እንገነዘባለን፡፡ ይልቁንም የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጾች ወይም መዋቅሮች፣ በፍችና በአጠቃቀም ወይም በአገልግሎት ላይ መሆን አለበት፡፡ ይህም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሙሉ እውቀትና የመግባባት ችሎታ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

## 2.4. የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ

### 2.4.1. ግልጽነት

አንድ የትምህርት ይዘት ጥሩ አቀራረብ አለው የሚባለው ግልጽ ሆኖ ሲቀርብ ነው፡፡ ከሰዋስው ትምህርት ይዘት አንጻርም ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በመረዳት ረገድ ምንም እክል ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው አይገባም ወይም የቀረበው የሰዋስው ትምህርትይዘት ከአቀራረብ አንጻር ለመረዳት አስቸጋሪ መሆን የለበትም (Harmer፣1987)፡፡ ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ የቀረቡ ገለጻዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትእዛዞችና መልመጃዎች ግልጽ እና የማያጠራጥሩ እንዲሆኑ ይመከራል፡፡

Swan (1994) ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ግልጽ መሆን እንዳለባቸው ይገልጻሉ። በመቀጠልም የምናቀርበው ይዘት ግልጽነት ይኖረው ዘንድ አቀራረባችን ተገቢውን ቅደም ተከተል የጠበቀ፣ ምሳሌዎችን ያካተተ፣ ለዋና ዋና ነጥቦች አጽንኦት የሰጠ፣ አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮችን ያስወገደ መሆን አለበት። የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ስለሚያቀርቧቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቂ ግንዛቤ አለመኖር አቀራረባቸው ግልጽነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ አዘጋጆች ስለሚያቀርቧቸው ይዘቶች በቂ ግንዛቤ ወይም እውቀት እንዲኖራቸውና ተማሪዎች ሊረዱ በሚችሉበት መልኩ በገለጻ እና በምሳሌዎች በመታገዝ ሊያቀርቡ ይገባል።

Sheldon (1988) እና Edege (1993) እንደሚገልጹት፣ በክፍል ስራም ይሁን በቤት ስራነት የሚሰጡ መልመጃዎች ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ሊኖራቸው ይገባል። በመልመጃዎች ስር ተካተው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ የሚያሳይ ግልጽ ምሳሌ መቅረብ አለበት። ይህም ተማሪዎች ላይ ግርታ እንዳይፈጠር ይረዳል።

### 2.4.2. ትክክለኛነት

Swan (1994) እንደሚገልጹት፣ ትክክለኛነት አውነተኛ የቋንቋውን ስነ-ልሳናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ይዘት ይመለከታል። ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ትክክልና እውነተኛ ሊሆኑ ይገባል። በእርግጥ የታላሚውን ቋንቋ አንዳንድ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ትክክለኛ ቅርጽ ማሳየቱ ከተማሪዎች እድሜና የትምህርት ደረጃ አንጻር ከባድና ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ይህ ሆኖም ግን በተቻለ መጠን ተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ ባህሪ እንዲያውቁት ያስፈልጋል፡ከገለጻው እንደምንገነዘበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ ስንሞክር ትክክልና እውነተኛ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ሲሆን፣ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ይዘትም የቋንቋውን እውነተኛ ስነ-ልሳናዊ ባህሪ የሚያሳይና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚቀበለው የቋንቋ አጠቃቀም እንደሆነ ነው።

### 2.4.3. ተመጣጣኝነት

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ከቋንቋው ክሂል ዘርፎች፣ ሰዋስው፣ቃላትና ስነ-ጽሁፍ ተመጣጥነው መሆን አለበት። የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚኖራቸው ስርጭት ከታላሚው ቋንቋ ልዩልዩ የሰዋስው ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ ጥረት

መደረግ አለበት። በዚህም መሰረት ይዘቶቹ ከቋንቋው የድምጽ ስርዓት፣ የምእላድና የቃል ክፍሎች፣ የአገባብና የፍች ስርዓት የተውጣጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል (Harmer፣1987)።

ከቀረበው ገለጻ የምንረዳው የሰዋስው ትምህርት አቀራረቡ ለተወሰኑ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ትኩረት መስጠት እንደሌለበትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች ማካተት እንዳለበት ነው። ይህም ሊፈጠር የሚችለውን አሰልችና አላስፈላጊ ድግግሞሽ ያለበት አቀራረብ እንዳይኖር አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

### 2.4.4. ተገቢነት

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች እድሜ ብስለት፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ቀደምት እውቀት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ አንጻር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው። ይዘቶቹ ከተማሪዎች የመገነዘብና የመስራት አቅም በላይ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ሆነው መዘጋጀት የለባቸውም (Sheldon፣1988)። ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋራ የተጣጣሙ በመሆኛቸው ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው ይችላሉ።

## 2.5. የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት

የይዘቶች አደረጃጀት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት የትኛው መከተል እንዳለብት የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም ይዘቶች እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል

ከዚህም በመነሳት አደረጃጃት ከቀላል ወደ ከባድ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ተጨባጭ ከሆነው ወደ ረቂቁ ወይም ተገላቢጦሻቸውን እንዲሁም ድግግሞሽን ይመለከታል ማለት ይቻላል (Nunan፣1988፤Cunningsworth፣1995)።

Tyler (1949) እና Taba (1962) እንደሚያስረዱት የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ማስገኘት ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ሊደራጁ ይገባል አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነትን የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል ። ተዋረዳዊ ግንኙነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚቀርቡ የትምህረት ይዘቶች ወይም ልምዶች የሚኖራቸውን ግንኙነት ያሳያል ።

ለምሳሌ በአስራ አንደኛ ክፍል የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በአስራ ሁለተኛ ክፍል ከቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ጋራ ያላቸው ግንኙነት የይዘቶችን ተዋረዳዊ ግንኙነት ያሳያል ። ይህም አስራ ሁለተኛ ክፍል የቀረቡ ይዘቶች በአስራ አንደኛ ክፍል የቀረቡትን መሰረት አድርገው የሚገነቡ እንደሆነ ያሳያል ።

በሌላ በኩል የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች ከአስራ አንደኛ ክፍል የታሪክ፣ የስነ -ዜጋ ወይም ከሌላ የትምህረት ይዘቶች ጋራ ያላቸውን ግንኙነት የይዘቶችን ወይም የትምህርት ልምዶችን ጎናዊ ግንኙነት ያሳያል ።

በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ተተኳሪ የሆነው የአደረጃጀት ስልት የይዘቶችን ተዋረዳዊ ግንኙነት የሚያሳየው አደረጃጀት ነው። የጥናቱ ትኩረት የተለያዩ የትምህርት አይነቶች ይዘቶችን ጎናዊ ግንኙነቶችን ሚመለከት ባለመሆኑ ጎናዊ ግንኙነት ከጥናቱ ውጭ ሆኗል። በተዋረዳዊ ግንኙነት ስርም ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፤ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚሉ የአደረጃጀት ስልቶችን እናገኛለን ።

### 2.5.1. ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው መቅረባቸውን ይመለከታል። ለምሳሌ በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምእራፍ አንድ ላይ የቀረበ ይዘት በዛው የክፍል ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ሌሎች ምዕራፎች ውስጥ ተደጋገሞ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው። ይዘቱ ተደጋግሞ ሲቀርብ ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሆን አለበት። በሌላ አገላለጽ ምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበው በቀጣይ ምዕራፍ ከቀረበው ጋራ ተመሳሳይ የቅለት ደረጃ ሊኖረው አይገባም (Tyler፣1949፣Taba፣1962)

ተከታታይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምን አይነት ቅደም ተከተል ሊደራጁና ከተማሪዎች እድገት አንጻር ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ሊቀርቡ እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። በተከታታይነቱ ውስጥ ድግግሞሽ ጠቀሜታ አለው ።

አንድ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አንድ ጊዜ ብቻ መቅረቡ በቂ አይደለም። ይልቁንም ተማሪዎችበተለያዩ ምዕራፎችና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊያገኙት ይገባል። ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ትምህረት ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱት እንዲካኑትና በተገቢው ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሉት ያስችላቸዋል። ድግግሞሹ በተለይም ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቀሜታ

አለው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስዋዊ ቅርጾች በአንድ ጊዜ ትምህርት ላይዙት ይችላሉ (Larson-Freeman፣1991፤Cunningsworth፣1995)፡፡

ከቀረቡት ገለጻዎች እንደምንረዳው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርቡት የሰዋስው ይዘቶች በዛው መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው መምጣታቸውን የሚያሳይ መሆን እንዳለበት ሲሆን ድግግሞሹ ኋላ የቀረበው ይዘት ቀድሞ ከቀረበው ይዘት ስፋቱና ጥልቀቱ እጨመረ ጠንከር ብሎ መቅረብ እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲማሯቸውና በተመሳሳይ ይዘቶች እንዳይሰላቹና ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

### 2.5.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሆኖም በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኝ አይደለም፡ ተለጣጣቂነት አንድ የትምህርት ይዘት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተደጋግሞ መምጣት የሚያሳይ ነው፡፡ ድግግሞሽ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረው ይዘቶቹ እየጠለቁና እየሰፉ መሄድ አለባቸው (Tyler፣1949)፤ (Taba፣1962)፡፡ ለምሳሌ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ልናስተምር አቀድን እንበል፣ በበዚህ መሰረት በቅድሚያ ለአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ነጻ ተውላጠ ስሞችን በማቅረብ ከመደብ፣ ከጾታና ከቁጥር አንጻር በተደጋጋሚ እናለማምዳቸዋለን፡፡ በማስከተልም በስድስተኛ፣ በሰባተኛና፣ በስምንተኛ ክፍሎች በግስ ላይ እየተቀጠሉ ባለቤትን፣ ተሳቢን የሚያመለክቱ አጸፋ ተውላጠስሞችን በተከታታይ ልናስተምራቸው እንችላለን፡፡

Nunan (1988) በበኩላቸው ቀጣይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ፣ ሳይቆራረጡ እርስ በርስ ተሳስረው መደራጀት እንዳለባቸው የሚያሳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህ ተለጣጣቂነታአው ከክፍል ወደ ክፍል እያደገና ጥልቀቱ እየጨመረ የሚሄድ ነው ይላሉ፡፡

የምሁራኑ ሀሳብ ሲጠቃለል ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከክፍል ወደ ክፍል ተደጋግመው መቅረብ እንዳለባቸውና ከክፍል ወደ ክፍል የይዘቶቹ ጥልቀትና ስፋት እያደገ መደራጀት እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ ይህ ድግግሞሽ ይዘቶቹ ሳይቆራረጡ ቀጣይነት ባለው መልኩና እርስ በርሳቸው ተሳስረው እንዲደራጁ ያስችላል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በተደጋጋሚ እንዲለማመዷቸው እድል ይሰጣል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አሳስፈላጊና አሰልች ይሆናል፡

### 2.5.3. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

በዚህ አደረጃጀት ስልት የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ አይቀርብም፡፡ በቅድሚያ ህግጋቱን ሊጠቀሙበት የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ፤ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በደንብ በማጤን የቋንቋው ህግጋት ምን ሊሁኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ፡፡ ከዚያም ግምታቸውን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ምላሾችን ከመምህራቸው ያገኛሉ፡፡ ይህ የአደረጃጀት ስልት የህጻናትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ የተከተለና ተፈጥሯዊ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ (Cunningsworth፣1995)::

Harmer (1987) እና Larson-Freeman (1991) በበኩላቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት እንዲያወጡ የሚያበረታታ ነው፡፡ በዚህ ስልት አንድ አዲስ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ሲቀርብ ምንም አይነት ገለጻ አይደረግም፡፡ ዋናኛ ትኩረቱም ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ምሳሌዎች በመነሳት ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችሏቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎች እንዲለዩ ማስቻል ነው፡፡ ሆኖም ከተማሪዎች እድሜና የትምህርት ደረጃ ፣ለትምህርት ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ረቂቅነት ወዘተ. አንጻር ይህንን የአደረጃጀት ስልት መጠቀሙ አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ መምህራን ይናገራሉ፡፡ ስለዚህም በሌላ አደረጃጀት ስልት ሊታገዝ ይገባል፡፡

Comment [h5]:

### 2.5.4. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

በዚህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል ከገለፃውበመነሳትም ህግጋቱን በተግባር ላይ ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህ መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በገለጻ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህም ገለጻው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣1995)::

Harmer (1987) እና Larson-Freeman (1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን አስመልክተው ያቀረቡት ገለጻ ከዚህ በላይ ከቀረበው ገለጻ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ በእነሱ አገላለጽ በዚህ የአደረጃጀት ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገለጻውንም መሰረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር ወደ መለማመድ

ያመራሉ። Stevick (1986) እንደሚያስረዱት ገለጻ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና ተማሪዎችን ለማገዝ አንድ መንገድ ነው። አላማውም ተማሪዎች ቋንቋውን ለተግባቦት በሚጠቀሙበት ወቅት ተገቢና ትክክለኛ ቅርጾችን በፍጥነትና በትክክል መምረጥ እንዲችሉ መረዳት ነው። ሆኖም ብቻውን በቂ ባለመሆኑ በደጋፊ ምሳሌዎች ሊታገዝ ይገባል።

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልቶችን በማወዳደር ይሄኛው ወይም ያኛው የተሻለ ነው። ይሄኛ ወይም ያኛው ትክክል ነው ማለት አይቻልም። ብቸኛ የሆነ አዋጭ አደረጃጀት የለም። ተማሪዎች እንደየባህሪያቸው በሁለቱ ስልቶች ሊማሩ ይችላሉ። ስለዚህም የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ሁለቱንም በማቀናጀት ሊጠቀሙባቸው ይገባል።

## 2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ባዩ ተሾመ (2004) "በደቡብ ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከስምንተኛ እስከ አምስተኛ ክፍል የአማርኛ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል አጥንቷል፡ የጥናቱም ትኩረት በተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ነበር። የሰዋስዋዊ ይዘቶችን አቀራረብ በተመለከተ በአራቱም ተተኳሪ መጽሀፎቸ ውስጥ ችግሮች መኖራቸው ተረጋግጧል። የይዘቶች አደረጃጀት በተመለከተም እንዲሁ ችግር እንዳለባቸው በጥናቱ ትንተና አሳይቷል።

ሁሉባንተ አደመ (1994) "በአማራ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ለሚገኙ ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ነበር። በግምገማው ውጤትም በመማሪያ መጻህፍቱ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ግልጽነት እንደሌላቸው፣ ከተማሪዎች ልምድና ችሎታ ጋር እንዳልተጣጣሙ፣ ከየሰዋስው ክፍሉ ተመጣጥነው እንዳልቀረቡ እንዲሁም አደረጃጀታቸው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንደሌላቸው አመልክቷል።

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) "በአዲስ አበባ ከተማና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋሰው አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ያቀረበው ጥናት ነው። ዓላማው የተጠቀሱት ሁለት ክልሎች በሚጠቀሙባቸው የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያመጻሕፍት ውስጥ የሰዋሰው  አቀራረብና አደረጃጀት በማነጻጸር ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን ነቅሶ ማውጣት ነው። ጥናቱን ከድምዳሜ ለማድረስም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ-መጠይቅና የሰነድ ምርመራ የተጠቀመ ሲሆን በውጤቱም ክልሎቹ መሰረት ያደረጉት አንድ አይነት መርሀ ትምህርት ቢሆንም በአቀራረብና በአደረጃጀታቸው መለያየታቸውን፣ ሁለቱም ክልሎች የሰዋስው የአቀራረብ መርሆችን ተከትሎ አለመተግበር፣ ከመርሀ ትምህርቱ የመውጣት ችግር የተደረሰባቸው ግኝቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ሰሚራ አሊ (2010) "በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም. ስራ ላይ በዋለው የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰውይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል አጥንታለች በጥናቱም፣ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረቦች ተመጣጣኝ ሆነው እንዳልቀረቡ ተረጋግጧል። ከይዘት ድግግሞሽ አንጻር አብዛሀኞቹ ጥሩ የሚባሉ ሲሆን፣ አንድ ጊዜ ብቻ ተከስተው የማይቀጥሉ ይዘቶች እንዳሉ ተገልጧል። ድግግሞሽ ከሚታይባቸው ግማሽ ያህሉ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የሚሄድና ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የተደራጁ እንደሆነ ተረጋግጧል።

ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ተተኳሪ ካደረጉትርዕሰ ጉዳይ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ። በክፍል ደረጃም በከፊል ይመሳሰላሉ። ይሁን እንጂ ልዩነትም አላቸው።የባዩ ጥናት ሁሉንም የአንደኛ ደረጃ እርከኖች መጻህፍት ተተኳሪ በማድረጉና በደቡብ ክልል የተጠና መሆኑ፣ ይህ ጥናት ግን አማርኛ ቋንቋ እንደ አፍመፍቻ በሚሰጥበት ክልል የተካሄደ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ።

የባዩ ጥናት ሁሉንም የአንደኛ ደረጃ እርከኖች መጻህፍት ተተኳሪ በማድረጉና በደቡብ ክልል የተጠና መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያለያያቸዋል።

ከሁሉባንተ ጥናት ጋር በትኩረት አቅጣጫቸው፣ በተተኳሪ የክፍል ደረጃዎች፣በሚካሄዱበት ክልል እንዲሁም በተተኳሪ መጽሀፎቹ የክፍል ደረጃ ይመሳሰላሉ። ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻህፍቱ ዘመን ይለያያሉ።

የሐዋዝ ጥናት የሁለቱን ክልሎች (የአማራና አዲስ አበባ) የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት በማነጻጸር ተመሳሳይነትና ልዩነታቸው አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለውን ዝምድና ፈትሿል፡፡ ይህ ጥናትግን አልፈተሸም፡፡እንዲሁም ንጽጽራዊ ጥናት አይደለም፡፡

ከሰሚራ ጥናት ጋር ይዘውት በተነሱት ርዕሰ-ጉዳይ ቢመሳሰሉም የሰሚራ ጥናት ተተኳሪ የክፍል ደረጃው ስምንተኛ ክፍል ብቻ መሆኑ፣ የተካሄደበት ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጀ መማሪያ መጽሀፍ ስለሆነ ልዩነት አላቸው፡፡ እንዲሁም የሰሚራ ጥናት አደረጃጀትን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ውጤት-ተኮር፣ ሂደት-ተኮር ቀጣይነትን ከተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት አንጻር ብቻ የገመገመ ስለሆነ በከፊል ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

በጥናቶቹ ግኝት እንደተረጋገጠው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀቶችና አቀራረብ ላይ ጉድለትእንዳለ ተጠቁሟል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የተጠቆሙ የሰዋስው ይዘቶች የአቀራረብና አደረጃጀት ችግሮች በ2015 ዓ.ም በአማራ ክልል ስራ ላይ በዋሉት የ7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ምን ይመስላ የሚለው ተተትኗል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ2015ዓ.ም ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል አማራኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀትን መተንተን ነው። ጥናቱ በአይነቱ ገላጭ የምርምር ስልት ነው። በመሆኑም የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊ የምርምር ዘዴ በገለጻ ተተንትነዋል።

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች በአማራ ክልላዊ መንግስት በ2015ዓ.ም በስራ ላይ የዋሉ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት በመሆናቸው ሰነድ ፍተሻ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል። በተጨማሪም በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰበውን ሀሳብ ለማጠናከር በክፍል ደረጃው ከሚያስተምሩ አራት መምህራን በቃለ-መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል። መጻህፍቱ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ቢመረጡ የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት ተገቢ ነው ተብሎ ስለታሰበ ነው። የመምህራን ናሙና በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጧል። የዞን እና የትምህር ቤት፣ አጥኝዋ የምትሰራበት በመሆኑ ከቅርበት አንጻር በአመች ናሙና ተመርጠዋል።

### 3.1.1. የናሙና አወሳሰድ

#### 3.1.1.1. የመፃህፍት ናሙና አወሣሰድ

ከአምስተኛ እስከ ስምንኛ ካሉት አራት የክፍል ደረጃዎች በርእሱ የተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻህፍት በዓላማ ተኮር ናሙና የተመረጡ ናቸው። አጥኝዋ ሁለቱን መፃህፍት ብቻ የመረጠችባቸ ምክንያት ከአንደኛ ደረጃ እርከኖች ከፍተኛዎቹ የእርከኑ ማጠናቀቂያ የክፍል ደረጃዎች በመሆናቸው በነዚህ የክፍል ደረጃዎች ያለውን የሰዋስው ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ ለማየት ስለታሰበና ከ4-6 ካሉት የክፍል ደረጃዎች በተሻለ ሰፋ ብሎ ይቀርብ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ነው።

ሌላው ምክንያት ሁሉም ቢካተቱ ሊበዙ ስለሚችሉና ጥናቱን ከዳር ለማድረስ የአቅምና የጊዜ ውስንነት የሚያጋጥም ስለሚሆን የሁለቱ የክፍል ደረጃዎች መፃህፍት ብቻ ተመርጠዋል።

#### 3.1.1.2. የዞን እና የከተማ ናሙና አወሳሰድ

በአማራ ክልል ውስጥ ከሚገኙዞኖች ውስጥ ሰሜን ወሎ ዞን አጥኚዋ የምትሰራበት በመሆኑ በአመች ናሙና ተወስዷል፡፡ ከሰሜን ወሎ ዞን ወረዳዎች ደግሞ ራያ ቆቦ አሁንም አጥኚዋ የምትሰራበት ወረዳ በመሆኑ በአመቺ ናሙና ተመርጠዋል፡፡

#### 3.1.1.3. የትምህርት ቤት ናሙና አወሳሰድ

በራያ ቆቦ ወረዳ ውስጥ በርካታ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ካሉት ትምህርት ቤቶች የሮቢት አንደኘኛ ደረጃና የጎብየ  አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመራጭ ሆነዋል፡፡ እነዚህ  ትምህርት ቤቶችከ አመችነታቸው አኳያ የተመረጡ ናቸው፡፡

#### 3.1.1.4. የመምህራን ናሙና አወሳሰድ

በተመረጡት ትምህርት ቤቶች 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው ትንሽ በመሆኑ ሁሉም በጠቅላይ ናሙና  ተመርጠዋል፡፡

### 3.1.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎ

#### 3.1.2.1. የሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ ሰነድ ግምገማ በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ትኩረት የመጽሃፍ ትንተና ላይ ወይም ሰነድ ላይ ስለሆነ ነው፡፡ የተተነተኑት ሰነዶች በ2015ዓ.ም. በአማራ ክልል ስራ ላይ የዋሉ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ናቸው፡፡ የሰነድ ፍተሻው በክለሳ ድርሳን ውስጥ በቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች ላይ ተመርኩዞ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

#### 3.1.2.2.  የቃለ-መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቁጥራቸው ጥቂት ከሆኑ መረጃ ሰጮች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑም በናሙና ከተወሰዱት ሁለት ትምህርት ቤቶች አራት መምህራን ቃለ-መጠይቁ ተካሂዷል፡፡ ዘጠኝ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው መረጃ በመሰብሰብ ትንተናውን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ መምህራኑ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ስለሰዋስው

ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ያላቸውን አስተያየት ማወቅ ይቻል ዘንድ የቃለ-መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ የጥያቄቹም ጭብጥበመማሪያ መጻህፍቱ የሰዋስው አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡

የቃለ-መጠይቆቹ በክለሰድርሳን የቀረቡ ንድፈ-ሀሰቦችን (ግልጽነት፣ትክክለኛነት፣ተገቢነት፣ተከታታይነት፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ተለጣጣቂነትን) መሰረት በማድረግ በአጥኝዋ ከተዘጋጁ በኋላ ሁለተኛ ዲግሪ ባለው መምር እንዲሁም በአማካሪ መምህር አማካኝነት ተገምግመዋል፡፡ በተሰጠው መጋቤ ምላሽ መሰረት ማሻሻያ ተደረጓል፡፡ ዘጠኝ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎችም ተዘጋጅተው ከመምህራን መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የቃለ-መጠይቆቹም ጭብጥ በሰዋስው ይዘቶች አቀራራብና አደረጃጀት ጽንሰ-ሀሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በመገኘት 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ቃለ-መጠይቁ ተካሂዷል፡፡

**ሰንጠረዥ 3.1፡- ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን አጠቃላይ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | ኮድ | የመምህራን ብዛት | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ | አገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሮቢትአጠ/አንደኛደረጃ ትምህት ቤት | ሀ | 1 | ወ | ዲግሪ | 8 | 18 ዓመት |
| 2 | | ሐ | 1 | ወ | ዲግሪ | 7 | 35 ዓመት |
| 3 | | መ | 1 | ወ | ዲፐሎማ | 7 | 10 ዓመት |
| 4 | ጎብየአ/አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት | ለ | 1 | ሴ | ዲግሪ | 8 | 10 ዓመት |

ከላይ ከቀረበው ሰጠረዥ እንደምንመለከተው ከአንዱ በስተቀር ሶስቱ መምህራን የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ ነው፡፡ እንዲሁም ረዘም ያለ የስራ ልምድ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ከዚህም መረጃ ሰጮቹ የተሻለ የእቀት ደረጃና የዳበረ ልምድ ያካበቱ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተመረጡት የተሻለ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡

## 3.2. የመረጃ ትንተና ዘዴ /ስልት

በዚህ ክፍል በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት በምእራፍ ሁለት ከቀረቡት የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው የተካሄደው ከሁለቱ መጻህፍት በዋናነት በሰነድ ፍተሻ፣ በተጨማሪም በቃለ-መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የትንተናው አካሄድም እያንዳንዱን የአቀራረብ መርህ በመምዘዝ መማሪያ መጻህፍቱን በክፍል ደረጃ ቅደምተከተላቸው እንዴት እንደቀረቡ ከመጻህፍቱ ማስረጃ እየተወሰደ ነው፡፡ አደረጃጀታቸውንም እንዲሁ ከቀረቡት የአደረጃጀት መርሆዎች አንጻር እንዴት እንደተተገበሩ ማስረጃ ከመማሪያ መጽሃፍቱ ላይ በመጥቀስ ትንተናው ተካሂዷል፡፡ ከትንተናው በመነሳትም በእያንዳንዱ የመተንተኛ መርህ ስር የውጤቱ ማብራሪያ ተቀምጧል፡፡

በተጨማሪማሪም ከመምህራን በቃለ-መጠይቅ የተገኙ ምላሾችም በመረጃ ትንተናው ክፍል በእያንዳንዳንዱ የአቀራረብና የአደረጃጀት ንድፈ-ሀሳብ ስር በማካተት በሰነድ ፍተሻ ከተገኙ የመረጃ ትንታኔዎች ቀጥሎ እየገቡ ተተንትነዋል፡፡ መረጃዎቹ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና የውጤት መብራሪያ

ይህ ክፍል ከሰነድ ፍተሻና ከመምህራን በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና የሚቀርብበትና ውጤት የሚብራራበት ነው፡፡ በቅድሚያ ግን ስለመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ገጽታ አጠር ያለ ቅኝት ቀርቧል፡፡

## 4.1. የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ ቅኝት

ተተኪ መማሪያ መጻህፍቱ በአማራ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ባለመብትነት በክልሉ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባኤ በ2015ዓ.ም የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጻህፍቱ ውጫዊ ሽፋን የፊትለፊት ገጽ ላይ አማርኛ የተማሪ መጽሀፍ ከሚለው በኋላ የክፍል ደረጃዎቹ ተቀምጠዋል፡፡ በመቀጠል አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የያዘ ትልቅ ክብ፣ ከክቡ ውስጥ ደግሞ የህዳሴው ግድብ ስዕል ተቀምጧል፡፡ከመጻህፍቱ የጀርባ ሽፋን ደግሞ እንዲሁ አማርኛ የተማሪ መጽሀፍ ከሚለው ርእስ በኋላ የክፍል ደረጃው ተቀምጧል፡፡ ከግርጌ አሳታሚው ድርጅት፣ ዋጋው፣ የትምህርት ሚኒስቴር ዓርማ ይገኛል፡፡ ከመጽሀፎቹ ውጫዊ ሽፋን ወደ ውስጣዊ ሽፋን ሲገባ የጥንቃቄ መልእክቶች፣ ርእስና የክፍል ደረጃው፣ አዘጋጆች፣አርታኢዎችና ሌሎችም መረጃዎች ይገኛሉ፡፡

### ሀ. የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ መመሪያ መፅሀፍ

በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውጫዊ ሽፋን ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ፣ ከውጫዊ ሽፋኑ ቀጥሎ የጥንቃቄ መልእክት፣አዘጋጆችና አርታኢዎችን የሚጠቁሙ መረጃዎች ይገኛሉ፡፡ በቀጣዩ ገጽ ደግሞ የመጽሀፉን ባለመብት የሚገልጽ መረጃ አለ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገጽ ማውጫ የሚገኝ ሲሆን፣ በቀጣዮቹ ተከታታይ አምስት ገጾች በቅደም ተከተል ጠቃሚ ምክር ለተማሪ ወላጆች፣ የመጽሀፉ መሰረታዊ መርሆዎች፣ የመጽሃፉ ይዘቶች አደረጃጀትት/ማዳመጥና መናገር፣ አቀላጥፎ ማንበብና አንብቦ መረዳት፣ቃላት፣ ሰዋስው፣ መጻፍ በሚል ተቀምጧል፡፡ መጽሀፉ የተዘጋጀው ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ይሁን ለአፍ-ፊት የተገለጸነገር የለም፡፡ መጽሀፉ 162 ገጾች፣ 10 ምእራፎች፣ 24 ምንባቦችና 156 መልመጃዎች ይዟል፡፡ ከነዚህም መካከል 57ቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ናቸው፡፡ አስራሁለት የሰዋው ገለጻዎች አሉ፡፡ ከአስሩም ምእራፎች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተውባቸዋል፡፡

## ሰ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

የዚህ መማሪያ መጽሀፍ የውጭ ገጽና ቀጥሎ በሮማን ቁጥር የተቀመጡት ገጾች ከሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መጽሀፉ 164 ገጾች፣10 ምእራፎች፣ 144 መልመጃዎች አካቶ ይዟል በመጽሀፉ ከተካተቱ የተለያ ይዘት ካላቸው መቶ አርባአራት መልመጃዎች መካከል ሰዋስው ላይ የተመሰረቱት ይዘቶች 59 ናቸው፡፡ በአስሩም እራፎች ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች ተካተውባቸዋል፡፡መጽሀፉ ስለ ተለያዩ ርእሶች የሚያወሱ በዝርውና በግጥም የቀረቡ አስር ርእሶችን መሰረት ያደረጉ ሰላሳ ምንባቦችና ዘጠኝ አጫጭር ገለጻዎች(ማስታዎሻዎች) አሉት፡፡ የሰዋስው ይዘት ላይ ትኩረት አድርገው የተጻፉ ገጻዎች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡

ሌላው በተተኳሪ መጽሀፎቹ ውስጥ የሚታየው የጋራ ባህርይ በሁለቱም የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችም ሆኑ ሌሎች ይዘቶች በልዩ ሊዩ የአቀራረብ ስልቶች መቅረብ መቻላቸው ነው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በገጸ፣ በአብዛሀኛው በምሳሌዎችና መልመጃዎች መልክ የቀረቡ ሲሆን፣ መልመጃዎቹ ደግሞ ዓረፍተ ነገር ጻፉ፣ አውዳዊ ፍች፣ተመሳሳይ ፍች፣ተቃራኒ ፍች ስጡ፣ለይታችሁ አውጡ፣አዛምዱ፣በተስማሚ ቃል ሙሉ፣ እስተካክላችሁ ጻፉ፣ ግለጹ፣ በተስማሚ ቃል ተኩ ወዘተ. የአቀራረብ ስልቶች በሁለቱም የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ታይተዋል፡፡

የመማሪያ መጻህፍቱን አጠቃላይ ቅኝት በተመለከተ አጠር ባለ መልኩ ማየት ይቻል ዘንድ የሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1፡- የመማሪያ መጻህፍቱ አጠቃላይ መረጃ

| መረጃዎች | የክፍል ደረጃ | |
|---|---|---|
| | 7ኛ | 8ኛ |
| የህትመት ዘመን | 2015 | 2015 |
| የገጽ ብዛት | 162 | 164 |
| የምእራፍ ብዛት | 10 | 10 |
| የመልመጃዎች ብዛት | 156 | 144 |
| የሰዋስው ትምህርት የቀረበባቸው ምእራፎች ብዛት | 10 | 10 |
| የሰዋስው ትምህርት ላይ የተመሰረቱ መልመጃዎች ብዛት | 57 | 59 |
| ዋጋ | አልተገለጸም | 249.29 |

## 4.2. የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1. ከግልጽነት አንጻር

**ሀ. የመልመጃ ትዕዛዞች ግልጽነት**

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው በሚገኙ የሰዋስው ይዘቶች ላይ አልፎ አልፎ ችግሮች እንደሚታዩበሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡ ለምሳሌ፡- በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተወሰኑ የመልመጃ ትእዛዞች፣ጥያቄዎች፣ የማስታወሻ ገለጻዎች፣የግልጽነት ችግር እንዳለባቸው ታይቷል፡፡ የግልጽነት ችግር ያለባቸው ምሳሌዎች በሁለቱም መጻህፍት አልተገኙም፡፡ በሰምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ደግሞ የተወሰኑ የግልጽነት ችግር ያለባቸው የመልመጃ ትእዛዞች እንዳሉ ለመረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሀ. ሰንጠረዡን በደብተራችሁ አሟልታችሁ ጻፉ**

| ስነ | ፀረ | ቤተ | ህገ | ተጣማሪ ቃላት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወባ | ህዝብ | መስጊድ |
| | | | | ደንብ | ስርዓት | ህዋስ |
| | | | | አረም | እድገት | ክህነት |
| | | | | ልቡና | ዜጋ | ክርስቲያን |
| | | | | ሰብል | ሰላም | መዘክር |

/7ኛ ክፍል፣ ገጽ፣31/

ከላይ በ‹‹ሀ›› ላይ በአስረጅነት የተወሰደው ትዕዛዝ ስንመለከት ጸረ፣ ቤተ፣ህገ ከሚሉ ቃላት ጋር ሊመሰረቱ የሚችሉ ድርብ ቃላትን እንዲመሰርቱ ታስቦ ነው፡፡ ነገር ግን ትእዛዙ “ሰንጠረዡን

አሚልታችሁ ጻፉ"። በሚል ብቻ ድፍን ብሎ የተቀመጠ በመሆኑ ተማሪዎች ሰንጠረዡን ምን በመስራት እንደሚያሚሉ በግልጽ አይናገርም። ምን በማድረግ እንደሚያሚሉ ስለማይገልጽ ግልጽነት ይጎድለዋል። በሰንጠረዡ የተሰጡትን ቃላት በማጣመር ድርብ ቃላት መስርቱ ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር። እነዚህን መሰል ትዝዛዞች በመጽሀፉ በርካታ ገጾች ውስጥ ይገኛሉ።ምሳሌ፡ -ገጽ12፣16፣50፣54፣70፣80፣82፣87፣92፣96፣102፣103፣137፣154። የሚከተለውን አስረጅ እንመልከት።

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ ጻፉ።

   ሀ. ናቸው እነዚህ በሬዎች።

   ለ. ልጅ እሷ ናት ጎበዝ።

   ሐ. ይህ ነው ጠረጴዛ።

   መ. ተመሪዎች ናቸውእነዚያ ጎበዘው።

/7ኛ ክፍል፣ገጽ፣92/

የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች በምናይበት ጊዜ የመጀመሪያው የአማርኛ ቋንቋን የዓረፍተነገር እቃቀር ተከትለው ባልተቀመጡበት ዓረፍተነገር ሊባሉ አይችሉም። በአስረጅነት የተወሰደውን አ ስንመለከተው ዓረፍተነገሮቹን የሚገነቡት ቃላት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አይደለም። ሆኖም የጥያቄው ትዕዛዝም የቃላቱን ቅደም ተከተል አስተካክለው ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ መልእክት አያስተላልፍም። የሚስተካከሉት አረፍተ ነገሮቹ ሳይሆን የቃላቱ ቅደም ተከተል በመሆኑ ይህን በሚገልጽ መልኩ መቀመጥ ነበረበት። ከላይ የቀረበውን ሃሳብ ለማረጋገጥም የክፍል ደረጃውን ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን በቃለመጠይቅ/ጥያቄ ቁ.2/ ጥያቄቀርቦላቸው ነበር። ጥያቄውም "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃ ትእዛዞች ምን ያህል ግልጽ ናቸው" የሚል ነበር። መምህር "ሐ" "ትእዛዞቹ አጠር ያሉና ግልጽ ናቸው" በሚል አስተያየታቸውን ሲሰጡ፣ መምህር "መ" ደግሞ፣ "አብዛኛዎቹ ትእዛዞች ድፍን ያሉና ግልጽነት የሌላቸው፣ መምህሩ ያብራሩላችሁ የሚሉ በመሆናቸው ተማሪዎች ብቻቸውን ሆነው ለመስራት ይቸገራሉ" ሲሉ ገልጸዋል። እንዲሁም አንድ አይነት ትእዛዞች ሲደጋገሙ ይስተዋላል በማለት ተጨማሪ ሀሳብ ሰጥተዋል። ይህ የተመሳሳይ ትእዛዞች መደጋገም ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራት መደጋገማቸውን አመላካች እንደሆነ ከምላሹ መረዳት ይቻላል።

በተደረገው ሰነድ ፍተሻ በስምንተኛ ክፍል የግልጽነት ችግር የታየባቸው ትእዛዞች አልታዩም፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን "በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃ ትእዛዞች ምን ያህል ግልጽ ናቸው"?

### ለ. የምሳሌዎች ግልጽነት ችግር

በሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የግልጽነት ችግር ያለባቸው ምሳሌዎች አልተገኙም፡፡ በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን "በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ ምሳሌዎች ምን ያህል ግልጽ ናቸው?" በሚል /በቃለ-መጠይቅ ተራ ቁ.1/ ተጠይቀው መምህር "ሐ" እና መምህር "መ" ግልጽነት የጎደላቸው ምሳሌዎች በመጽሀፉ ውስጥ የሉም የሚል ነው፡፡ የመምህራኑ ምላሽ የሰነድ ፍተሻውን ትንተና የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

Comment [h6]:

Comment [h7]:

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የግልጽነት ችግር ያለባቸው ምሳሌዎች እንደሌሉ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራንም "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃ ምሳሌዎች ምን ያህል ግልጽ ናቸው"? በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ/ተራ ቁ.1/ መምህር "ለ" እና መምህር "ሀ" በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ግልጽነት የጎደላቸው ምሳሌዎች የሉምሲሉምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

### ሐ. የሰዋስዋዊ መልመጃ ጥያቄዎች እና የማስታወሻ ገለጻዎች የግልጽነት ችግር

የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍን ለመፈተሽ እንደተሞከረው የግልጽነጽ ችግር ያለበት አንድ ብቻ ገጽ18 ላይ ተገኝቷል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ ሰዋሰዋዊ መልመጃ ጥያቄዎች አቀራረብ ከግልጽነት አንጻር እንዴት እንደቀረቡ ይመለከቷቸዋል በሚል ለቀረበው ቃለ መጠይቅ/ተራ ቁ.1/ "ሐ" እና "መ" የሰጡት ምላሽ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የግልጽነት ችግር ያለባቸው መልመጃዎችና ማስታወሻዎች ያልተገኙ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ በአስረጅነት ከተጠቀሰው ውጭ የግልጽነት ችግር የሚታይባቸው ሌሎች ሰዋስዋዊ የመልመጃ ጥያቄም ይሁን የማስታወሻ ገለጻ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አልታየም፡፡ በሰነድ ፍተሻው የተገኘውን አስረጅ ቀጥለን እንመልከት

1.ጥንዶቹን ዓረፍ ነገሮች አጣምራችሁ አንድ ሙሉ ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ጋሻው በሰዓቱ ስራውን አጠናቀቀ፡፡

ጋሻው በጊዜ ወደቤቱ አመራ፡፡

ለ. ፋጡማ ከጓደኞቿ ጋር ተባበረች፡፡

ፋጡማ ስራዋን በጥሩ ሁኔታ ታከናውናለች፡፡

ሐ. አቶ ሙሳ የቀበሌያችን የጤና ባለሙያ ነው፡፡

አቶ ሙሳን ስለቤተሰብ ምጣኔ እጠይቀዋለሁ፡፡

መ. ልጅቷ ጠንክሮ አጠናች፡፡

ልጅቷ አንደኛ ወጣች፡፡

/7ኛ ክፍል ፣ገጽ፣18/

ከላይ በአስረጅነት የቀረቡት ዓረፍተነገሮች ትእዛዙ እንደሚገልጸው በጥገኛ መስተጻምር ተጣምረው እንድ ሙሉ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ለማጣመር “መ” ላይ ከተሰጡት ዓረፍተነገሮች የመጀመሪያው ዓረፍተነገር ሰዋስዋዊ ስህተት አለበት፡፡ ስህተቱም “ጠንክሮ” የሚለው ቦዝ አንቀጽ ከባለቤቱ/ልጅቷ/ ጋር በጾታ፣ከማሰሪያ አንቀጹ /አጠናች/ ጋር ደግሞ በመደብ አልተስማማም፡፡ የመጀመሪያው ዓረፍተነገር ሰዋስዋዊ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ስህተቱ ሳይስተካከል ሁለቱን ዓረፍተነገሮች እንደሌሎቹ ችዓረፍተ-ነገሮች ለማጣመር ተማሪዎች ይቸገራሉ፡፡ ከጥያቄ”መ” በስተቀር እዚሁ መልመጃ ላይ የቀረቡት ሌሎች አምስት ጥንድ ዓረፍተነገሮች ግን ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው በመሆኑ ተማሪዎች ሳይደናገሩ በቀጥታ ዓረፍተ-ነገሮቹን ማጣመርና አንድ ሙሉ ዓረፍተነገር ለመመስረት አይቸገሩም፡፡

በሰነድ ፍተሻው የሰዋስዋዊ ጥያቄዎችና የማስታወሻዎች የግልጽነት ችግር በ8ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ አንድ ጥያቄ ገጽ ሰ42 ችግር ያለበት እንደሆነ ታይቷል፡፡ የሰዋዋዊ ማስታወሻዎችና ጥያቄዎች ግልጽነት በሚመለከት በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ለሁለት መምህራን ቃለመጠይቅ/ጥያቄ ተራ ቁ.1/ መምህር "ሀ" እና "ለ"፣ "አልፎ አልፎ የማስታዎሻዎች ግልጽ ያለመሆን ችግር ይታያል፡፡ ማለትም የቀረቡት የማስታዎሻ ገለጻዎችና ማብራሪያዎች ለቀረቡት

ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቂና ዘርዘር ያሉ ካለመሆናቸው የተነሳ ግልጽነት ይጎድላቸዋል፡፡ በመሆኑምበተማሪዎች ዘንድ ምን ማለት ነው በሚል ጥያቄ የሚያስነሱ የማስታወሻ ገለጻዎች አሉ" የሚል ሲሆን፣የግልጽነት ችግር ያለባቸው ጥያቄዎች ግን እንደሌሉ ሁለቱም መምህራን ገልጸዋል፡፡ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ የግልጽነት ችግር ያለባቸው ጥያቄዎች አልተገኙም፡፡ ከመጽሀፉ የተወሰደውን ችግር ያለበትን የሰዋስዋዊ መልመጃ ጥያቄ አስረጅ ቀጥለን እንመልከት፡፡

2. በተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ ጊዜ አመልካች ቅርጾችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ሙሀመድ መጽሀፍ ይገዛል፡፡ መ.መልካሙ ነገ ይመጣል፡፡

ለ. መሰረት ስራ ትሰራለች፡፡ ሠ. ፈንታነሽ ታስተምራለች፡፡

ሐ. ረ. ዘይነባ ምሳ ትበላለች፡፡

/8ኛክፍል፣ ገጽ42/

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከላይ በአስረጅነት ከቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች ውስጥ በ"ሠ" ፣እና በ"ረ" በተሰጡት ጥያቄዎች ዓረፍተነገሮቹ ሙሉውን /ከባለቤቱ እስከ ማሰሪያ አንቀጹ ድረስ/ ተሰምሮባቸዋል፡፡ በሌሎቹ ጥያቄዎች ውስጥ ግን በትክክል ጊዜን በሚያመለክቱ ቃላት /ግሶች/ ስር ተሰምሯል፡፡በሁለቱ ጥያቄዎች ውስጥ በትእዛዙ የተገለፀውን ነገር አናገኝም፡፡ የተሰመረው ጊዜ አመልካች ቃሉ ላይ ሳይሆን ዓረፍተነገሮቹ ላይ ነው፡፡ስለሆነም በጥያቄዎቹ /ሠ እና ረ/ ላይ የተሰመረው መስመር በትክክለኛ ጊዜን በሚያመለክቱ ግሶች ላይ ባለመሆኑ ተማሪዎች በትእዛዙ እንዲሰሩ የታዘዙትን ተገንዝበው ለመስራትም ይሁን ጥያቄውን ለመረዳት ውዝግብ ውስጥ ይገባሉ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ የግልጽነት ችግር ያለበትን የማስታወሻ አስረጅ በመውሰድ እንመለከታለን፡፡

ማስታወሻ

የመሆን ግስ የሚባሉት ስምን በመሙያነት የሚወስዱ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- እነዚህ ዋልያዎች ናቸው፡፡ በሚለው ዓረፍተነገር ናቸው የመሆን ግስ

ሲሆን፣ዋልያዎች የሚለው ስም ደግሞ ለመሆን ግሱ መሙያ ነው፡፡

/7ኛ ክፍል፣ ገጽ 92/

ከዚህ ማስታወሻ ቀጥሎ አምስት የስም መሙያ ያላቸው አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ታዘዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከላይ ስለመሆን ግስ እና ስለመሙያ የቀረበው ማስታወሻ እና ምሳሌ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ካለመሰጠቱ የተነሳ ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡ በቀላሉ የመሆን ግስ የሚባሉት ነው፣ናቸው...ተብሎ በነዚህ ግሶች የሚያስሩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ ቢባል ግልጽ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች ለመስራት አይቸገሩም፡፡ የቋንቋው ቅርጽ ሳያውቁት ስምንም ቅጽልንም በመሙያነት ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረት መመስረት ይችላሉ፡፡ ግንዛቤ ማስጨበጥ የተፈለገው ስለመሆን ግሶች ስለሆነ ስምን በመሙያነት የሚወስዱ ናቸው ባይባል ይሻላል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህር "መ" ና መምህር "ሐ" "የሰዋስዋዊ ማስታወሻ ገለጻዎች ከግልጽነት አኳያ እዴት ይገልጧቸዋል? /ጥያቄ ቁ.1/ በሚል ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ መምህር "ሐ" እና መምህር "መ" የሰጡት ምላሽ "አጭርና ግልጽ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ወደፊት ስለሚሰሯቸው መልመጃዎች ፍንጭ የሚሰጡና ስለሚማሩት ህግ ግንዛቤ የሚየስጨብጡናቸው"፡፡ የሚል ነው፡፡

Comment [h8]:

### 4.2.2. ከትክክለኛነት አንጻር

ትክክለኛነት እውነተኛውን የቋንቋ ስነ ልሳናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪሰ ማህበረሰብ ሰየሚጠቀምበትን ይዘት የሚመለከት ሀሳብ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተገልጧል፡፡ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎች ስህተት የሚያስተምሩ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በማስከተል ተተኳሪ መጽሀፍቱ ከዚህ ንድፈሀሳብ አንጻር ያላቸውን ገጽታ ለማሳየት ይሞከራል፡

በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ገጽ 71 አንድ የሰዋስዋዊ ማስታወሻ ገለጻ ትክክለኛነት ችግር ይገኛል። በስምንተኛ ክፍል ግን አልታየም። እነዚህንም አስረጅዎችን በመውሰድ ለማሳየት ይሞከራል።

ሀ. የሰዋስዋዊ ይዘት ገለጻ ትክክለኛነት ችግሮች

> **ማስታወሻ**
>
> ሳቢ ግስ የሚባለው ግሱ ቀጥተኛ ተሳቢ የሚፈልግ ከሆነ ነው።
>
> ቀጥተኛ ተሳቢ የሚታወቀው በቃሉ መድረሻ ላይ "ን" የሚል የተሳቢ ምልክት ሲጨመርበት ነው። ለምሳሌ፡- ልጅቷ ልብሷን ቀደደች
>
> ኢሳቢ ግስ የሚባለው ግሱ ቀጥተኛ ተሳቢ የማይፈልግ ከሆነ ነው።
>
> ኢሳቢ ግስ ያለምንም ተሳቢ ይነገራል። ምሳሌ ልጁ ተኛ።
>
> 7ኛክፍል፣ገጽ፣71

ስለሳቢና ኢሳቢ ግስ ለማብራራት ሲባል፣ "ቀጥተኛ ተሳቢ የሚታወቀው በቃሉ መድረሻ ላይ "ን" የሚል ተሳቢ ምልክት ሲጨመርበት ነው"። የሚለው የማስታወሻ ገለጻ ሁልጊዜ ትክክለኛና አዋጭ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም "-ን" ተሳቢ ጠቋሚ የምትሆነው የግድ በምትገባበት ቦታ ነው።ይሁን እንጅ ቀጥተኛ ተሳቢ ባላቸው ሁሉም አረፍተነገሮች ልትጨመር አትችልም። ከዚህ አንጻር ቀጥተኛ ተሳቢ የሚታወቀው በቃሉ መድረሻ ላይ "ን" ሲጨመርበት ነው የሚለው ትክክለኛ ገለጻ አይመስልም። "-ን" የግድ የምትጨመረው ተሳቢ ሆኖ የገባው ስም

- የተጸውኦ ስም ከሆነ
- የእምርነት አመልካች/ኡ/ ከተቀጠለበት እና በሌሎችም ምክንያቶች እንደሆነ የታወቃል።

ስለሆነም ከላይ ከተገለጹት ውጭ ሆነው በተሳቢነት የገቡ ስሞች "-ን" ን አይጨምሩም ማለት ነው። ሌላው ችግር "ን" አሁን ባለችበት ሁኔታ ፊደል እንጅ ተሳቢ አመልካች ምእላድ አይደለችም። ተሳቢነትን የምታመለክተው "-ን" በዚህ መልክ ስትቀመጥ ነው። በዚህ መልክ

ብትቀመጥም እንኳ ቀጥተኛ ተሳቢ የሚታወቀው በቃሉ መድረሻ ላይ “ን” ሲጨመርበት ነው የሚለው ትክክለኛ ገለጻ አይደለም፡፡

ለምሳሌ፡- “ግንበኛው በመዶሻ ድንጋይ ፈለጠ፡፡” የሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ እንደሚታየው ተሳቢ አለው፡፡ ነገር ግን ተሳቢው ላይ አስፈላጊ ስላልሆነች /ከላይ የተገለጹት ምክንያቶች ተሳቢ ሆኖ በገባው ስም ላይ ስለሌሉ/ “-ን” አልተጨመረችም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በእንደዚህ ዓይነት ዓረፍተ ነገር ውስጥ ተሳቢን ለመለየት ይቸገራሉ ወይም “-ን” ን እየፈለጉ ይውላሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ከላይ ስለቀጥተኛ ተሳቢ የቀረበው የማስታወሻ ገለጻ ተማሪዎችን፣ ተሳቢ ሁልጊዜ በስተመጨረሻ “-ን” የተጨመረበት ስም ነው ወደሚል ማጠቃለያ ስለሚያደርሳቸው ትክክለኛና ዘላቂ ሰዋስዋዊ ገለጻ አይደለም፡፡

ከዚህ አንጻር የተሳቢን ምንነት ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሳቢ ማለት በኣረፍተነገር ውስጥ በግሱ የተገለጸው ድርጊት የሚፈጸምበት/ ድርጊት ተቀባይ የሆነ/ ስም ነው ተብሎ ቢቀርብ የተሸለ ይሆናል፡፡ “-ን” የግድ በገባችበት ቦታ ተሳቢ አመልካች ናት የሚለው እንደተጨማሪ ተሳቢን የመለያ ዘዴ ቢሆን የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ለሁለት የክፍል ደረጃው “መምህራን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘት ገለጻ ከትክክለኛነት አንጻር እንዴት ይታያል? /ጥያቄ ቁ.5/” በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ የመምህር "ሐ" እና የመምህር "መ" ምላሽ ስህተት የሆነ የሰዋስዋዊ ይዘት ገለጻ እንደሌለ የሚገልጽ ነው፡፡ በተደረገው የሰነድ ፍተሻም እንደተረጋገጠው ከላይ በአስረጅነት ከቀረበው ውጭ የትክክለኛነት ችግር የሚታይበት ሰዋስዋዊ ገለጻ እንደሌለ ነው፡፡

Comment [h9]:

### 4.2.3. ከተመጣጣኝነት /ሚዛናዊነት አንጻር

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከታላሚው ቋንቋ ስነድምጽ፣ ስነምዕላድ፣ የስነአገባብና ስነፍች የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተውጣጥተው የቀረቡ መሆን እንዳለባቸው በክለሳ ድርሳን ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በእርግጥ እንደ ተማሪዎቹ አይነት፣ የክፍልና የእውቀት ደረጃ፣ ፍላጎት፣ የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ለአንዳንድ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ከሌሎቹ የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በተቻለ መጠን ይዘቶቹ ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች የሚዳስሱ እንዲሆኑና በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች መቅረብ እንዳለባቸው ይመከራል፡፡

ከዚህ ንድፈሀሳብ አንጻር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ መጻህፍት ምን ገጽታ እንዳላቸው ቀጥሎ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ይህን ለማድረግም ያመች ዘንድ ሥለመጻህፍቱ የሰዋስው ይዘት ስርጭት ሁኔታ የሚገልጽ ሰንጠረዥ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

***ሠንጠረዥ 4.2፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ***

| ተ.ቀ | የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች | የክፍል ደረጃና የሰዋሰው ክፍሎቹ የስርጭት መጠን | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ ክፍል | | 8ኛ ክፍል | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስነ-ድምጽ | - | - | - | - |
| 2 | ስነ-ምእላድ | 12 | 19.4 | 20 | 23.8 |
| 3 | ስነ-አገባብ | 25 | 40.3 | 27 | 32.1 |
| 4 | ስነ-ፍች | 25 | 40.3 | 37 | 44.1 |
| 5 | ጠቅላላ ድምር | 62 | 100 | 84 | 100 |

ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው የሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ከስነድምጽ በስተቀር ሶስቱን የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች አካቷል፡፡ ይህም አንድ የሚዛናዊነት ችግር እንዳለ ያሳየናል፡፡ ሌላው የተካተቱትን የሰዋሰው ይዘቶችም ስናይ ተመጣጣኝ ሆነው አልቀረቡም፡፡ በመጽሀፉ ውስጥ ከተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ስነፍች እና ስነአገባብ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው 40.3% የሚሆነውን ሽፋን አግኝተዋል፡፡ ከዚህም የሁለቱ የሰዋስው ክፍሎች ተመጣጠኝነት ጥሩ እንደሆነ ትንተናው ሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የስነ-ምእላድን ሽፋን መመልከት እንደሚቻው ከሁለቱ በግማሽ በማነስ 19.4% በመያዝ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን፣ "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ከልዩልዩ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ ከመቅረብ አንጻር ምን ገጽታ አላቸው?" በሚል ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ /ጥያቄ ቁጥር3/ መምህር *"መ"* "ከሁሉም የሰዋስው ክፍሎች የተመጣጠኑ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ስለስነ-ድምጽ ምንም የቀረበ ይዘት የለም" የሚል

ነው፡፡ አክለውም በመጽሀፉ ውስጥ የቃላት ዐውዳዊ ፍች እንደሚበዛ የገለጹ ሲሆን፣ መምህር "ሐ" ደግሞ "ከሁሉም የሰዋስው ይዘቶች የተውጣጡ ናቸው" ካሉ በኋላ አውዳዊ ፍች እንደሚበዛ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ  የምንረዳውም የይዘት አለመመጣጠን እንዳለ ነው፡፡

የቀረበውን የሽፋን መመጣጠን በምናይበት ጊዜ ለስነ-ድምጽ ምንም ሽፋን አልተተውም፡፡ ለዚህ ምክንያት ሊሆን ሚችለው የስነድምጽ የሰዋስው ክፍል ሰፊና ውስብስብ ስለሚሆን ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ ለክፍል ደረጃዎቹ በሚመጥን መልኩ በቃላት ውስጥ ላልተውና ጠብቀው ስለሚነበቡ ድምጾች ማንሳት ሚቻል ሳይሆን አይቀርም፡፡ ስነ-ምእላድ ደግሞ ከስነ-አገባብና ከስነ-ፍች በግማሽ ዝቅ ብሎ ይገኛል፡፡ ስነ-አገባብና ስነ-ፍች እኩል የሽፋን መጠን ይዘዋል፡፡ ከዚህም በሁለቱ መካል ፍትሀዊ መመጣጠን እንዳለ ያስረዳል፡፡ ባጠቃላይ ከመረጃው መገንዘብ እንደሚቻለው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ይዘቶች ሽፋን ያልተመጣጠነና ከነጭራሹም የተዘነጋ የሰወዋስው ክፍል እንዳለ ነው፡፡ በተካተቱት የሰዋስው ክፍሎችም ቢሆን በውስጣቸው ከሚገኙ ንዑሳን ይዘቶች ውስጥ ጠቂቶቹን ብቻ እንዳካተቱና መካተት የሚገባቸው ንዑሳን ይዘቶች ሳይካተቱ መቅረታቸውን ከታች የቀረበው ዝርዝር የሰንጠረዥ መረጃ ያሳያል፡፡

እንዲሁ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች የመመጣጠን ችግር ይታያል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ በድጋሚ ስነድምጽ ምንም ሽፋን ያልሰጠው ነው፡፡ ከተካተቱት ሶስት የሰዋስው ይዘቶች ስነምእላድ ዝቅተኛ ሽፋን የተሠጠው ሲሆን 23.8% ሽፋን አግኝቷል፡፡ ስነአገባብ 32.1% በመያዝ በሁለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስነፍች በመጽሀፉ ውስጥ ከፍተኛውን ሽፋን የያዘ ሲሆን 44.1% ሽፋን ተሰጥቶታል፡፡ ትንተናው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች ተመጣጣኝ ሆነው እንዳልቀረቡ ያሳያል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መመህራንም፣ "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ልዩልዩ ሰዋስዋዊ ክፍሎች በተመጣጠነ ሁኔታ ከማካተት አንጻር ምን ገጽታ አላቸው? /ጥያቄ ቁጥር 3/" በሚል ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ሁለቱም የሰጡት ምላሽ  በመጽኀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ከሁሉም የሰዋስው ክሎች የተውጣጡ እንዳልሆኑና ስነ-ድምጽንም በሚመለከት የቀረበ ይዘት እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቃላት ዐውዳዊ ፍች እንደሚበዛ ጠቁመዋል፡፡

### 4.2.4. ከተገቢነት አንጻር

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት አላቸው የሚባለው ከተማሪዎች እድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የቀደመ እውቀት ወዘተ. ጋር የሚጣጣሙ ሆነው ሲቀርቡ እንደሆነ በክለሳድርሳናችን ክፍል አንስተናል፡፡ከዚህ አንጻር በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ መማሪያ መጻህፍት ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው ቀጥሎ በቅደም ተከተል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

#### ሀ. የ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ

በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ሙሉለሙሉ ለማለት በሚያስችልሁኔታ ከተማሪዎች የመስራት፣የመገንዘብ አቅም በላይ ሆነውአልተገኙም፡፡

በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተገቢነትን በሚመለከት (ጥያቄ ቁ.4) ለተደረገላቸው ቃለመጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህር "መ" በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋው ይዘቶች ከተማሪዎች አቅም አኳያ ተገቢ እንደሆኑ ነው፡፡ እንዲያውም ከመስራት አቅማቸው በታች ስለሆኑ ቢጨመር የሚል ነው፡፡ መምህር " ሐ" እንዲሁ ከተማሪዎች የመስራት አቅም ጋር ተመጣጣኝ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

#### ለ. የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

በስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከአንድ ይዘት በስተቀር ሌሎች ሰዋስዋዊ ገለጻዎች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ሲፈተሹ ከተማሪዎች የመስራትና የመገንዘብ አቅም በላይ እንደማይሆኑ በሰነድ ፍተሸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህር "ሀ" እና "ለ" ተገቢነትን በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሁለቱም መልስ ከተማሪዎች የመስራት አቅም በላይ አይደሉም የሚል ነው፡፡የተገቢነት ችግር አለበት ተብሎ የታሰበው ይዘት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

1.በ"ሀ" እና በ"ለ" ረድፍ የቀረቡ ቃላት የሚለያዩባቸውን ቅርጾችና የቅርጾቹን ፍች ተናገሩ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ሰበረ | ይሰብራል |
| ቀነሰ | ይቀንሳል |
| መከረ | ይመክራል |

2. በተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ ጊዜ አመልካች ቅርጾችን ለይታችሁ ጻፉ

ሀ.ሙሀመድ መጽሀፍ ይገዛል መ.መልካሙ ነገ ይመጣል

ለ.መሰረት ስራ ትሰራለች ሠ. ፈንታነሽ ታስተምራለች

ሐ. ሀሊማ መጽኀፍ ትጽፋለች ረ. ዘይነባ ምሳ ትበላለች

/ 8ኛ ክፍል፣ገጽ41-42/

ከላይ በማስረጃነት ስለቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ከመልመጃ ጥያቄዎቹ በፊት ጊዜ የኃላፊ፣ የአሁን፣ የትንቢት ጊዜ ተብሎ እንደሚከፈል የማስታወሻ ገለጻ ከነምሳሌው ተሰጥቷል። እንዲሁም ቋንቋዎች የግድ ጊዜን በሶስት ላይከፍሉ ይችላሉ። ለምሳሌ አማርኛ ቋንቋ የአሁንና የትንቢት ጊዜን አንድ አድርጎ ኢኃላፊ ጊዜ ብሎ ነው የሚከፍለው። ስለሆነም አማርኛ ቋንቋ ጊዜን የሚከፍለው ኃላፊና ኢኃላፊ ብሎ እንደሚከፍል በማስታወሻው ተገልጧል። ከዚህ ሌላ ስለጊዜ አመልካች ቅርጾችና የቅርጾች ፍች የቀረበ ገለጻም ይሁን ምሳሌ የለም።ይዘቱ ትንሽ ጠጠር ያለ ነው።ይህ በሆነበት ተማሪዎች ይዘቱን መገንዘብም ሆነ መልመጃውን መስራት ይችላሉ ብሎ ማሰብ ከባድ ነው።ስለዚህአጥኝዋ ለዚህ ይዘት በቂ የሆነ ገላጻም ይሁን ምሳሌ ካለመሠጠቱም ባሻገር ለዚህ የክፍል ደረጃ የማይጥን ነው የሚል ሀሳብ አላት።

Comment [h10]:

በመልመጃ ጥያቄዎቹ እንዲሰሩ የተፈለገው በትእዛዝ አንድ ስር የጊዜ አመልካች ቅርጾቹን እንዲለዩና ፍቹን የሃላፊና ኢሃላፊ ብለው እዲናገሩ ታስቦ ይመስላል። በሁለተኛው ትእዛዝም እንዲሁ ጊዜ አመልካች ቅርጾችን ከተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ ለይተው እንዲጽፉ ነው። ይሁን እንጂ ስለጊዜ አመልካች ቅረጾቹ ወይም በግሶች ላይ ስለሚጨመሩ ምእላዶች በተመለከተ የተሰጠ ምሳሌም ይሁን ገለጻ በዚህ የክፍል ደረጃም ይሁን ካለፈው የክፍል ደረጃ የተነሳ ነገር የለም።ይህም ቢሆን እንኳበግሶቹ ውስጥ የተጨመሩ የጊዜ አመልካች ቅርጾችን ለይቶ ማውጣትውሰብስብና ሰፊ ይዘት በመሆኑ ለዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች የሚመጥን አይደለም፡

## 4.3. የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1. ከተከታታይነት አንጻር

በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተገለጸው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ በተለያዩ ምእራፎች ውስጥ ተደጋግመው መቅረብ

እንዳለባቸውና ድግግሞሻቸውም ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይ ጽንሰሀሳብ ነው። ድግግሞሹ ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶቹን በሚገባ እንዲረዷቸው፣ እንዲካናቸውና በተገቢ ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሏቸው ያስላቸዋል። ከዚህ አንጻር የጥናቱ ተተኳሪ መጻህፍት ምን ገጽታ እንዳላቸው እናያለን። በቅድሚያ ግንበሁለቱም መጻህፍት ውስጥ ተካተው የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶችን የድግግሞሽ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ እንመለከታለን።

**ሠንጠረዥ 4.3፡- በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መጻህፍት ውስጥ ተከታታይነት አግኝተው የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችና የድግግሞሽ መጠን**

| የሰዋስው ይዘቶች በአብይ ክፍል ደረጃ | የሰዋስው ይዘቶች በንኡስ ክፍል ደረጃ | የክፍል ደረጃና የድግግሞሽ መጠን በቁጥርና በመቶኛ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ ክፍል | | | 8ኛ ክፍል | | |
| | | የሚገኙበት ገጽ | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | የሚገኙበት ገጽ | ብዛት በቁጥር | በመቶ ኛ |
| ስነ-ድምጽ | -------- | --- | | | ------ | --- | --- |
| ስነ-ምእላድ | ድርብናተዛማጅ ቃላት ምስረታ | 31 | 1 | 1.6 | 39፣54፣73፣ 84፣95፣ 107፣112፣ 129፣139፣ | 9 | 10.46 |
| | ባለቤትና ማሰሪያአንቀጽ | 9፣38 | 2 | 3.22 | 14፣36 | 2 | 2.3 |
| | ስም፣ቅጽል፣ግስ፣ ተ/ግስ/ቃልክፍል/ | 50፣155 | 2 | 3.22 | 98104 | 2 | 2.3 |
| | ተውላጠስም፣መደብ አመልካች ምእላድ | 54፣59፣142 | 3 | 4.83 | 76 | 1 | 1.16 |
| | ሳቢና ኢሳቢ ግስ | 71 | 1 | 1.6 | ---------- | --- | --- |
| | የመሆን ግስ | 92 | 1 | 1.6 | | | |
| | ባለቤት ከነንዙ፣ማሰሪያንቀጽ ከነንዙ | 161 | 1 | 1.6 | ------- | ---- | ---- |
| | የግስ ባህሪ/ጊዜ/ | 142 | 1 | 1.6 | 31፣41፣42፣ 71፣118 | 5 | 5.81 |
| | የስምና የግስ ገላጭ | ----- | ----- | ---- | 20 | 1 | 1.16 |
| ስነ-አገባብ | አያያዥ ቃላት | 23፣27፣87 | 3 | 4.83 | ------- | ---- | --- |
| | በጥገኛ መስተጻምር ዓረድተነገሮችን ማያያዝ | 18 | 1 | 1.6 | -------- | --- | --- |
| | ጠቋሚመስተዓምር | 43 | 1 | 1.6 | ------- | ---- | ---- |
| | አወንታዊ፣አሉታዊ፣ ጥያቂያዊ፣አጋናኝ፣ትእዛዛዊ ዓ፣ነገሮች | 67፣77፣81፣ 98፣103፣ 108፣149 | 7 | 11.3 | 5፣9፣14፣ 81፣86፣91፣ 108፣123 | 8 | 9.3 |
| | ዓረፍተነገር ምስረታ | 12፣53፣107 | 3 | 4.83 | 54፣47፣155 | 3 | 3.48 |
| | የተጓደሉዓረፍተነገሮችን ሰማሟላት | 36፣70፣102 | 3 | 4.83 | 44፣54፣89፣ 96፣140 | 5 | 5.81 |

Comment [h11]:

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮችን ማስተካከል | 92 | 1 | 1.6 | 51 | 1 | 1.16 |
| | ሰዋሰዋዊ ግድፈት ያለባቸውዓረፍተነገሮችን ማቃናት | ------ | ---- | ---- | 46 | 1 | 1.16 |
| | ዓረፍተነገሮችን ወደጥገኛ ሀረግ መለወጥ | ----- | ---- | --- | 55፣27 | 2 | 2.32 |
| | ነጠላ ዓረፍተነገሮችን አጣምሮ ድርብ ኣረፍተ ነገር መመስረት | 115 | 1 | 1.6 | 60 | 1 | 1.16 |
| | ጅምር ዓረፍተነገሮችን መቋጨት | 120 | 1 | 1.6 | -------- | ---- | ---- |
| | ጥንድ ዓረፍተነገሮችን በማጣመር ውስብስብ ዓረፍተነገሮች መመስረት | 125፣131፣ 137 | 3 | 4.83 | 66፣136፣ 141 | 3 | 3.48 |
| | ጥገኛ ሐረግን መለየት | ---- | ----- | ---- | 131፣148፣ 163 | 3 | 3.48 |
| | ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መለየት | 137 | 1 | 1.6 | 60፣163 | 2 | 2.3 |
| ስነ-ፍች | የቃላት ተመሳሳይ ፍች | 8፣75፣86፣ 90፣118 | 5 | 8.1 | 3፣34፣38፣ 59፣64፣74፣ 161 | 7 | 8.1 |
| | የቃላት ቀጥተኛ ፍች | 26፣64፣65 | 3 | 4.83 | 13፣18፣65 | 3 | 3.48 |
| | ቃላት ፍካሬያዊ ፍች | 65 | 1 | 1.6 | ---- | ---- | ---- |
| | የቃላት አውዳዊ ፍች | 4፣16፣22፣ 26፣41፣47፣ 80፣96፣112፣ 123፣129 | 11 | 17.74 | 8፣13፣26፣ 30፣59፣64፣ 69፣79፣84፣ 107፣112፣ 116፣129፣ 135፣140፣ 146፣154 | 20 | 23.25 |
| | ቃላትን ከማብራሪያቸው ጋር ማዛመድ | 57 | 1 | 1.6 | ------- | --- | ---- |
| | የሐረጋት አውዳዊ ፍች | 135 | 1 | 1.6 | 19፣26፣30፣ 50 | 4 | 4.65 |
| | የዓረፍተነገሮች አውዳዊ ፍች | 135 | 1 | 1.6 | ------ | ----- | --- |
| | የቃላት ተቃራኒ ፍች | 12፣16 | 2 | 3.22 | 45፣95፣155 | 3 | 3.4 |
| | ጠቅላላ ድምር | 27 ሰዋስዋዊ ይዘቶች | 62 | 100 | 21 ሰዋስዋዊ ይዘቶች | 86 | 100 |

### ሀ. የ7ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

በሰንጠረዥ ሶስት ላይ እንደሚታየው በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አስራአንድ ጊዜ(17.74%) በተለያዩ ምእራፎች ውስጥ በመደጋገም ከፍተኛ ሽፋን የያዘው የቃላት አውዳዊ ፍች የሚለው

ይዘት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው የዓረፍተነገር አይነቶች/አወንታዊ፣አሉታዊ፣ ጥያቄያዊ፣ትእዛዛዊ፣መጠይቃዊ ዓረፍተ-ነገር /የሚለው ይዘት ሲሆን፣ በመማሪያ መጽሀፉ በተለያዩ ምእራፎች ውስጥ ሰባት ጊዜ (11.3%) ተደግሟል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ተደጋግመው የምናገኛቸው የቃላት ተመሳሳይ ፍች አምስት ጊዜ (8.1%) ተደግሟል፡፡ ስድስት ይዘቶች /ተውላጠስም፣ አያያዥ ቃላት፣ ዓረፍትነገር ምስረታ፣ የተጓደሉ ዓረፍ-ተነገሮችን ማሟላት፣ ጥንድ ዓረፍተነገሮችን ወደ ውስብስብ ዓረፍተነገር መቀየር፣ የቃላት ቀጥተኛ ፍች የሚሉት ይዘቶች እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስትጊዜ (4.8%) ተደግመዋል፡፡ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ፣ የቃል ክፍሎች (ስም፣ግስ፣ቅጽል፣ተ/ግስ)፣ የቃላት ተቃራኒ ፍች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ(3.2%) ተደጋግመዋል፡፡ ቀሪዎቹ አስራአምስት ይዘቶች 55.5% የሚሆነውን ሽፋን የያዙት አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ ናቸው፡፡

ከትንተናው መረዳት እንደሚቻለው በመጽሀፉ ውስጥ ሀያሰባት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አስራሁለቱ (44.4%)የሚሆኑት ይዘቶች በተለያየ መጠን የተደጋገሙ ሲሆን፣ አስራአምስቱ (55.5%) ይዘቶች ግን አንድ ጊዜ ብቻ ብቅ ብለው የጠፉ ናቸው፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የተለጣጣቂነት ችግር መኖሩን ያሳያል፡፡ እንደዚህ አይነቱ ችግር ተማሪዎች ቀረቡላቸውን ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተደጋጋሚ እንዲለማመዱ ሰፊ እድል የማይሰጥ በመሆኑ ይዘቶችን በደንብ ለመረዳት እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ የተለያዩ ምእራፎች ውስጥ ተደጋግመው ከመቅረብ አንጻር ምን አይነት ገጽታ አላቸው/ጥያቄ ቁጥር 5/ በሚል ለሁለት መምህራን የተጠየቀ ሲሆን፣መምህር "ሐ" አልፎ አልፎ ተደጋግመው የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዳሉ የገለጹ ሲሆን፣መምህር "መ" ደግሞ ብዙ ይዘቶች ተደጋግመው እንደሚመጡ ገልጸዋል፡፡ የይዘት ድግግሞሹ ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድን አስመልክቶ ደግሞ መምህር "መ" በተከታታይነት የቀረቡ ይዘቶች አልፎ አልፎ ስፋትና ጥልቀታቸው እንደሚጨምር የገለጹ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ግን ምንም ቅርጽ ሳይቀየር አሰልች የሆነ ድግግሞሽ የሚታይባቸው እንደሆነ ጨምረው ገልጸዋል፡፡ መምህር"ሐ ደግሞ የሚደጋገሙ ይዘቶች እንደ ተማሪዎቹ አቅም ሰፋ ብለውና ጥልቀታቸው ጨምሮ የቀረቡ ናቸው ሲሉ ምላሻቸውን ሠጥተዋል፡፡

## ለ. የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ሃያአንድ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ ከፍተኛ የድግግሞሽ መጠን የያዘው ልክ እንደሰባተኛ ክፍሉ የቃላት አውዳዊ ፍች ነው፡፡ ይዘቱ በመማሪያ መጻሀፉ የተለያዩ ምእራፎች ውስጥ ሃያጊዜ (23.8%) ተደጋግሟል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የሚገኘው ስለድርብ ቃላት /ተዛማጅቃላትን/ በተመለከተ የቀረበው ይዘት ሲሆን፣በመጽሀፉ የተለያዩ ምእራፎች ውስጥ ዘጠኝ ጊዜ (11.9%) ተደጋግሟል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ተደጋግሞ የሚገኘው የዓረፍተነገር ዓይነቶች (አወንታዊ፣ አሉታዊ፣ ጥያቄያዊ…) የሚለው ይዘት ሲሆን፣ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ስምንት ጊዜ (9.5%) ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ የቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰባት ጊዜ (8.3%) በመደጋገም በአራተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችንና አንቀጾችን ማሟላት፣ የግስ ባህሪ/ጊዜ/ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ጊዜ (5.95%) ተደጋግመዋል፡፡ጥገኛ ሐረግን መለየት፣የሐረጋት አውዳዊ ፍች እያንዳንዳቸው አራት አራት ጊዜ (4.76%) ጊዜ ተደጋግመዋል፡ ሶስት ይዘቶች እያንዳንዳቸው ሰስት ሶስት ጊዜ (3.6%) ተደገሙ ሲሆን፣አራት ይዘቶች ደግሞ ሁለትሁለት ጊዜ (2.4%) የተደጋገሙ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አምስት ይዘቶች አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል፡፡

ባጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት ሃያአንድ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደሰባተኛ ክፍሉ ከፍተኛ የድግግሞሽ ሽፋን የተሰጠው የቃላት አውዳዊ ፍች ነው፡፡ ይዘቱ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ሃያ ጊዜ (23.8%) ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ስለድርብ ቃላት የቀረበው ይዘት ዘጠኝ ጊዜ (11.9%) በመደጋገም በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በሶስተኛ ደረጃም የዓረፍተ ነገር አይነት ስምንት ጊዜ (9.5%) ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ የቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰባት ጊዜ (8.3%)፣ የግስ ባህሪ/ጊዜ/፣ የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን ማሟላት እያንዳንዳቸው አምስት ጊዜ(5.95%) የተደጋገሙ ናቸው፡፡ ሁለት ይቶች አራት አራት ጊዜ (4.76%)፣ሶስት ይዘቶች እያንዳንዳቸው ሶስትሶስት ጊዜ (3.57%)፣ሁለት ይዘቶች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ (2.4%) ተደጋግመው እንደቀረቡ የመረጃው ትንተና ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በመጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት ሃያ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ አምስቱ ይዘቶች (25%) ወይም አንድ አራተኛ ያህሉ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ እንደሆኑ ትንተናው ያሳያል፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራንም በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተደጋግሞ መቅረብንበሚመለከት ለቀረበላቸው ቃለመጠይ (ጥያቄ ተ.ቁ 5) መምህር

"ለ"የሰጡት ምላሽ አንዳንዶቹ ተደጋግመው የቀረቡ እንደሆኑ፣አንዳንዶቹ ደግሞ ያልተደጋገሙም እንደሆኑና ስፋትና ጥልቀታቸውም እየጨመረ እንደማይሄድ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡መመህር "ሀ" ደግሞ "አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩ ምእራፎች ሲከታተሉ አይታዩም::" የሚል ነው፡፡ ከዚህ በተያያዘ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ ስለመሄዱ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ (ጥያቄ ተ.ቁ 6) የይዘቶች ድግግሞሽ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የጥልቀቱንና ስፋቱንም መጨመር ማየት ይቸግራል፡፡ የተደጋገሙትም ቢሆን ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ የማይታይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ሃያአንድ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል አስራ-ስድስቱ (76.1%) የሚሆኑት በተለያየ መጠን ተደጋግመው የቀረቡ መሆኑን ከትንተናው ተመልክተናል፡፡ ይሁንእንጅ ተደጋግመው የቀረቡትም በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ የድግግሞሽ መጠን ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህም ማለት አንዱ ይዘት ከፍተኛ የድግግሞሽ መጠን ሲኖረው፣ የተወሰኑት ላይ ደግሞ ዝቅተኛ ድግግሞሽ እንዳለ ይታያል፡፡ በአንጻሩም አንድ ጊዜብቻብቅ ብለው የሚጠፉም አምስት ይዘቶች (25%) እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ በመማሪያ መጽኀፉ ውስጥ የይዘቶቹን ተከታታይነት በተመለከተ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ የይዘቶቹን የስፋትና የጥልቀት ሁኔታዎችን ደግሞ ቀጥሎ ከመጽሀፉ አስረጅ በመውሰድ እንይ፡፡

በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከተካተቱ ይዘቶች ውስጥ ከፍተኛ የድግግሞሽ መጠን የተሰጠው የቃላት አውዳዊ ፍች ነው፡፡ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት ጨምሮ ያለመቅረብ ሁኔታ ይታያል፡፡ቀጥሎ ለዚህ በአስረጅነት የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች እንመልከት፡፡

ለምሳሌ፡-

1.ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ዐውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ህብረቀለማት ሐ.ቀልሳ ሠ. ወዝውዞ

ለ. ዝማሬ መ. መጣር ረ. መማረክ

/7ኛ ክፍል፣ገጽ4/

1. ለሚከተሉት ቃላት ዐውዳዊ ፍች ጻፉ፡፡

ሀ. ምኞት ሐ. ማስጠናት ሠ. ልብ አለ

ሰ. ድጋፍ　　　መ. መጣር　　　ሰ. ኃላቀር

/7ኛ ክፍል፣ገጽ16/

1.ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ጻፉ፡፡

ሀ. መክፈል　　ሐ. ጠባይ　　ሠ.ማስተናበር

ለ. መታቀፍ　　መ. አስተዋጽኦ

/7ኛክፍል፣ ገጽ41/

ከላይ በአስረጅነት የተወሰዱት የአውዳዊ ፍች መልመጃዎች በተለያዩ ምእራፎችና ገጾች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በሶስቱም አስረጅዎች የቀረቡት የቃላት አውዳዊ ፍች መልመጃዎች ስንመለከታቸው የመጀመሪያውና በሶስተኛ የተቀመጡት በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ናቸው፡፡ ሁለቱም በተመሳሳይ መንገድ የሚሰሩ ናቸው በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው ከምን ተነስተው አውዳዊ ፍች እንደሚጠጡ የሚገልጽ ነገር የለውም፡፡ እንዲሰሩ የታዘዘው ነገር የቃላቱን አውዳዊ ፍች ጻፉ የሚል ብቻ ነው፡፡ ሶስቱም አስረጅዎች ላይ በአንድ አይነት ትእዛዝ የሚሰሩ ስራዎች ናቸው የተሰጡት ብዙም እድገት ሲጨምር የማያሳይ በመሆኑ የስፍትና ጥልቀት ችግር ይታይበታል፡፡ ስለሆነም ድግግሞሹ አሰልች ድግግሞሽ ነው፡፡ በተመሳደሳይ ሁኔታ ስለቃላት ተመሳሳይ ፍች በገጽ 8፣75፣86፣90፣118 የቀረቡት መልመጃዎች የስፋትና የጥልቀት ችግር የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ ቀሪ ይዘቶች ብዙ ድግግሞሽ የሌላቸው በመሆኑ ድግግሞሽ በሌለበት ጥልቀት ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

ባጠቃላይ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተደጋግመው ያለመቅረብና ጥልቀታቸውና ስፋታቸውም ከምእራፍ ምእራፍ እያደገ ያለመሄድ ችግር እንዳለ በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በ8ኛ ክፍል መጽኀፍ ከቀረቡ ይዘቶች ስፋትንና ጥልቀት በሚመለከት በገጽ 44፣54፣89 ስለየተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ የቀረቡትን መልመጃዎች ብናይ ሶስቱም ላይ ምንም ልዩነት አያሳይም፡፡ ዓረፍተ ነገሮች ተሰጥተዋል ሁሉምላይ ቃላትና ሐረጋትን መርጠው እንዲያሟሉ ያሚያዙ ናቸው፡፡ የቃላት ክብደትም ይሁን ስፋት ሲጨምር አይታይም፡፡ በተጨማሪም በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ስለድርብ ቃላት ወይም ተዛመጅ ቃላት በተመለከተ የቀረበው ይዘት በመጽሀፉ ውስጥ እስከ ዘጠኝ ጊዜ ተደጋግሟል፡፡ ድግግሞሹም በተሻለ ሁኔታ

ላይ ይገኛል፡፡ የጥልቀት ችግር ያለበት ይዘት ከዚህ ሌላ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አልታየም፡፡ ድግግሙሽና ጥልቀት እየጨመረ የመሄዱ ጉዳይ የሰተሻለ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

#### 4.3.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት፣ የሰዋሰው ይዘቶች ተከታታይነት ባላቸው የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ተደጋግመው ወይም ተለጣጣቂነት ባለው መንገድ ተደራጅተው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ጽንሰሃሳብ እንደሆነ በክለሳ ድርሳን  የተገፅው ሃሳብ ያስረዳል፡፡ እንዲሁም ተከታታይነቱ ከክፍል ክፍል እያደገና ስፋትና ጥልቀቱ እየጨመረ መሄድን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ መርሆ አንጻር ተተኳሪ መጻህፍቱ ምን ገጽታ እንዳላቸው አጥኝዋ በመዳሰስ ተከታዩን ጉዳይ አስቀምጣለች፡፡

በሰንጠረዥ 4.3 መረዳት እንደሚቻለው ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በአጠቃላይ ሰላሳ አንድ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቀርበው ይገኛሉ፡ ከነዚህ መካከል አስራ ሰባቱ (54.8%) በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ ያለምንም መቆራረጥ በተከታታይ ቀርበዋል፡፡ ግማሽ የሚጠጉት አስራ አራቱ (45.1%) ደግሞ በመጻህፍቱ ውስጥ በተለጣጣቂ ተደራጅተው የመቅረብ ድክመት እንደሚገኝባቸው በሰንተረዥ 4.3 ከቀረበው መረጃ ያስገነዝበናል፡፡ ለምሳሌ ሳቢና ኢሳቢ ግስ(71)፣የመሆን ግስ(ገጽ92)፣ ባለቤት ከነጓዙና ማሰሪያ አንቀጽ ከነጓዙ(ገጽ161)፣ አያያዥ ቃላት(ገጽ23፣27)፣ በጥገኛ መስተዓምር ዓረፍተነገሮችን ማያያዝ(ገጽ18 በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ እንጂ በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ ይህም ይዘቶቹ በየክፍል ደረጃዎቹ በቀጣይነት እንዳልቀረቡ ያሳያል፡፡አልፎ አልፎ ደግሞ በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ተካተው በሰባተኛ ክፍል ያልተካተቱ ይዘቶች እንዳሉ ከሰንጠረዡ ማትየ ይቻላል፡፡ ይህንንም ጉዳይ ለማረጋገጥ በቃለመጠይቅ የክፍል ደረጃውን ለሚያስተምሩ መምህራን ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡ መምህር "ሐ" በመማሪያ መፅሃፍቱ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተከታታይነት አላቸው የሚል ነበር፡፡

የመምህር "መ" ምላሽ፣ "በእኔ እምነት አብዛኛዎቹ የሰዋስው ይዘቶች ተከታታይነት አላቸው ተማሪዎች ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ናቸው፡፡" ስፋትና ጥልቀታቸውን አስመልክቶ የመምህር "ሐ" ምላሽ፣ "አልፎአልፎ  ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የሚሄድ አለ፡፡ አብዛኛዎቹ ይዘቶች ግን ምንም ቅርጽ ሳይቀየር አሰልች ድግግሞሽ ሲደጋገም

ይታያል"፡፡ ያሉ ሲሆን መምህር "መ" ደግሞ፣ "ይዘቶች ሲደገሙ እንደተማሪዎች አቅም ሰፋ ብሎና ጥልቀታቸው ጨምሮ ነው"፡፡ በማት ገልጸዋል፡፡

ስምንተኛ ክፍል ለሚያስተምሩ ሁለትመምህራን "በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች የደረጃው ተማሪዎች ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ናቸው?" በሚል ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ መምህር "ሀ"፣ "ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ይዘቶች ከዚህ በፊት ባሉ የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ናቸው፡፡" የሚል ሲሆን፣ መምህር "ለ"፣ "መጽሀፎቹ አዲስ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ይዘቶቹን ከዚህ በፊት የተማሯቸው እንደሆኑ ተማሪዎች ይጠቁሙናል" ሲሉ ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡ ስፋትና ጥልቀትንም በሚመለከት መምህር "ሀ"፣ "የይዘት ድግግሞሹ ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ ሲሄድ አይታይም" ይላሉ፡፡ መምህር "ለ"ም "የይዘት ድግግሞሹ አናሳ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ጥልቀቱንም ማግኘት አይቻልም፡፡ አንዳንድ የተደጋገሙ ይዘቶችም ቢሆን ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ሲሄዱ አይታዩም፡፡" የሚል ነው፡፡ ቀጥለን ደግሞ ከመጻህፍቱ አስረጅ በመውሰድ እንመለከታለን፡፡

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አሟልታችሁ ጻፉ

| ሐረግ | ስም | ቅጽል | ተ/ግስ | ግሰ |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. ጥቁር አንበሳ<br>ለ. ግምኛ ሄደች<br>ሐ. ክፉ ሰው<br>መ.<br>ሠ.<br>በ. ነጭ ጃኬት | | | | |

/7ኛ ክፍል፣ገጽ50/

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተውሳከግስ የሆኑ ቃላትን አውጥታችሁ ጻፉ

ምሳሌ፡- ዘርፌ ትናንት ደስተኛ ነበረች፡፡

ሀ. መስፍኔ መላኩ ነገ ወደ ጋይንት ይሄዳል፡፡

ለ. አዝመራው ሲሳይ ገና ይደሰታል

/8ኛ ክፍል፣ገጽ 104/

ከላይበተተኳረ መጻህፍቱ በአስረጅነት ከተወሰዱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ማየት እንደሚቻለው የቃል ክፍሎችን ለማስተማር ታስቦ የቀረቡ መልመጃዎች ናቸው፡፡ በየክፍል ደረጃዎቹ ተለጣጣቂነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በስምንተኛ ክፍል የቀረበው ስፋትና ትልቀት ጨምሮ አልቀረበም፡፡ እንዲያውም ተውሳከግስን ብቻ አቅርቦ ሌሎቹን በሰባተኛ ክፍል ያሉት ሰፋ አድርጎ አቅርቧቸው ነበር፡፡ በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ግን ቀርተዋል፡፡ ይህም ስፋቱና ጥልቀቱእየጨመረ አለመሄዱን ያሳያል፡፡

### 4.3.3 . ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

ይህ የአደረጃጀት መርህ ተማሪዎች ስለሚማሩት ህግ በቅድሚያ ገለጻ ወይም ማብራሪያ አይሰጥም፡፡ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምሳሌዎችና መልመጃዎች ብቻ በመንተራስ የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት ወይም ስርዓት ለይተው እንዲያውቁና እንዲለማመዱ የሚበረታቱበት ስልት ነው፡፡ የሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በዚህ አደረጃጀት ስልት የተደራጁ ጥቂት የዘቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከዝዝር ወደ አጠቃላይ ስልት የተደራጁ ስእንደሆኑ በፍተሻው ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከእያንዳቸው የክፍል ደረጃ አስረጅ በመውስድ ለማየት ይሞከራ፡፡

#### ሀ.ሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

የሚከተሉትን ዓረፈተነገሮች በብዙ ቁጥር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ጻፉ

ምሳሌ፡ - አበበ ከትምህርት ቤት ተመለሰ

-እነ አበበ ከትምህርትቤት ተመለሱ

ሀ. አርሶ አደሩ ሰብል በመሰብሰብ ላይ ነው፡፡

ለ.ደራሲዋ መጽሀፍ አስመረቀች፡፡

/ 7ኛ ክፍል ገጽ 38/

ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡ ውሀው <u>ደፈረሰ</u>፡፡ (ቆሸሸ)

የህዝቡ ሰላም ደፈረሰ፡፡ (ታወከ)

የጓደኛዬ አይን ደፈረሰ፡፡ (ቀላ)

ሀ. በደረሰበት ሀዘን ምክንያት አይኖቹ አንባ አፈሰሱ፡፡

ለ. ልጆቹ ከግቢው ያለውን ውሃ ወደ ውጭ አፈሰሱ፡፡

/7ኛ ክፍል፣ገጽ 112/

በአስረጅነት የቀረቡትን ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ስንመለከት መጀመሪያው አስረጅ ላይ በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ባለቤት ሆነው የገቡ ስሞችንና ማሰሪያ አንቀጾችን ምሳሌውን ተንተርሰው እንዲሰሩ በማድረግ የባለቤትና ግስ በቁጥር መጣጣምን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡ በሁለተኛው አስረጅ ደግሞ አፈሰሱ የሚለው ቃል በተለያየ ዓረፍተነገር ሲገባ የተለያየ ፍች እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ ከዚህም ተማሪዎች አንድ ቃል በተለያየ ዓረፍተነገር ውስጥ(ዐውድ) ሲገባ የተለያየ ፍች እንደሚኖረው ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ ቀጥሎም ይህንግንዛቤ በመያዝ በመልመጃ እንዲለማመዱ ወደሚያስችላቸው ተግባር ይጓዛሉ፡፡ ይህ አቀራረብ ስለአውዳዊ ፍች መጀመሪያ ላይ ያቀረበው ገለጻ የለም፡፡በምሳሌዎችና መልመጃ በማለማመድ አንድ ቃል በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ሲገባ የተለያየ ፍች አለው ወደሚለው መደምደሚያ የሚያሸጋግራቸው ነው፡፡ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ እንደተቻለው በመጽሀፉ ውስጥ ቢዚህ የአደረጃጀት ስልት የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ጥቂት አንደሆኑና በገጽ 23፣ 80፣81፣120፣123፣161 ላይ የሚገኙት ብቻ እንደሁኑ ተረጋግጧል፡፡

በደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎች የተደራጁት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ነው? ወይስ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር? የትኛው በስፋት ይገኛል? በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ/ተራ ቁ.3/ የሰጡት ምላሽ መምህር "መ" አብዛኛው ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የተደራጁ እንደሆኑና የተወሰኑም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ተደራጁ እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ ሁለተኛውም ተጠያቂ መምህር "ሐ" ሁለቱም አደረጃጀቶች ያሉ ቢሆንም በመጽሀፉ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት በስፋት እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡ ይህን ሲያብራሩም በመጀመሪያ ስለሚማሩት ህግ ገለጻ /ማስታወሻ/ ይሰጣል ከዚያም መልመጃዎቹን እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በክለሳ ድርሳን ለማንሳት እንደተሞከረው አንድ ብቸኛና አዋጭ የአደረጃጀት ስትልት የለም ሚል ነው። ስለሆነም የሰባተኛ ክፍል *መማሪያ መጽሀፍ* ውስጥ ይዘቶች በአብዛኛው የተደራጁት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር  በሆነ የአደረጃት ስልት ነው። ይህ ደግሞ ለተማሪዎች አሰልችነት ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም የተለያዩ የአደረጃጀት ስልቶች ተቀናጅተው ቢቀርቡ ጠሩ ይሆን ነበር።

### ለ. ስምንተኛ ክፍል አማርኛ *መማሪያ መጽሀፍ*

ከላይ እንደተገጸው የስምንተኛ ክፍል አማርኛ *መማሪያ መጽሀፍ* ውስጥ ሁለቱም የአደረጃጀት ስልቶች የተካተቱበት ነው። ይሁን እንጂ ከዝርዝር ወደአጠቃላይ የአደረጀጀት ስልት በስፋት እንደሚታይ በፍተሻው ተረጋግጧል።ተማሪዎች በተለያዩ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ውስጥ የቀረቡላቸውን ምሳሌዎችን ብቻ በማየት የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ የሚያዙ በርካታ ይዘቶች በ*መማሪያ መጽሀፉ* ውስጥ ይታያሉ። ቀጥሎ ከመጽሀፉ ውስጥ በአስረጅነት የተወሰደውን የሰዋስው ይዘት እናያለን።

1. አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ

ምሳሌ፡-      አዎንታዊ                                                  አሉታዊ

- መስከረም ጥሩ መጽሀፍ ገዝታለች።          - መስከረም ጥሩ መጽሀፍ አልገዛችም።

2.የሚከተሉትን ግሶች በሁለተኛ እና በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ጻፉ

ምሳሌ፡-   <u>ግስ   2ኛ መደብ ብዙ ቁጥር3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር</u>

| | | |
|---|---|---|
| ወሰደ | ወሰዳችሁ | ወሰዱ |
| ሰነቀ | ሰነቃችሁ | ሰነቁ |

ሀ. ከፈተ                 ለ. መከረ

በሰባተኛ ክፍል እንደታየው ሁሉ በስምንተኛ ክፍል  *መማሪያ መጽሀፍም* ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘት መልመጃዎች በቅድሚያ ለተማሪዎች ምሳሌዎችን አቅርበዋል። ተማሪዎችም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በመመርኮዝ የመልመጃ ጥያቄዎችን ይሰራሉ። ከምሳሌዎቹና ከመልመጃ ጥያቄዎች በሂደት ስለአወንታዊ፣ አሉታዊ ዓረፍተነገሮች እና በክፍል ደረጃቸው በሚመጥን መልኩ የሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የግስ ቅጾችን ህግጋት ወደመገንዘብ

ይሸጋገራሉ። ይህ መጽሀፍ በርካታ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አካቶ እንደያዘ በፍተሻው ታይቷል። ምሳሌ፡- በገጽ 9፣14፣20፣23፣36፣ 39፣41፣60፣64፣71፣74፣81፣86፣91፣98፣104፣135፣148 ናቸው።

በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን መጽሀፉ የተደራጀው ከዝርዝር ወደአጠቃላይ ነው? ወይስ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አደረጃጀት? የትኛው ስልት በስፋት ይታያል? በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ (ተራ.ቁ፣9) መምህር "ለ"አብዛኛው የመጽሀፉ አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንደሆነ፣ አልፎ አልፎ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትም እንደቀረበ /አንዳንዶቹ ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ጥያቄ ከመስራታቸው በፊት ሊማሩት ስለታሰበው ህግ ገለጻና ምሳሌ ይሰጥና መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያዛል/ በማለት የገለጸ ሲሆን፣ ሌላኛው መላሽመምህር "ሀ"“እኔ እንዳየሁት መጽሀፉ ውሰጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት በስፋት ይታይበታል።” የሚል ነው።

### 4.3.4. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

በዚህ አደረጃጀት ስልት በቅድሚያ ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ህግ የሚያሳይ ገጻ በበቂ ምሳሌ ተደግፎም ይቀርባል። በማስከተልም ተማሪዎች በገለጻ የቀረቡላቸውን ሰዋሰዋዊ ይቶች በዝርዝር ወደ መለማመድ ያመራሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢም በተተኳሪ መጻህፍቱ ውስጥ በዚህ ስልት የተደራጁ የሰዋስው ይዘቶች መኖራቸውን አረጋግጧል።

#### *ሀ. የ7ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ*

በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አስራሶስት የሰዋስው ገለጻዎች ተካተው ይገኛሉ። እነዚህም ስለ ባለቤትና ማሰሪያ አንቅጽ (ገጽ 9)፣ ስለጥገኛ መስተዓምር (ገጽ18)፣ ስለጠቋሚ መስተዓምር (ገጽ 42)፣ ስለቅጽልና ተውሳ ከግስ (ገጽ 49)፣ስለተውላጠስም መደብ (ገጽ54)፣ስለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች (ገጽ 64)፣ ስለአዎንታዊና አሉታዊዓ.ነገር (ገጽ67፣81)፣ ስለሳቢና ኢሳቢ.ግስ (ገጽ71)፣ ስለ የመሆንግስ (ገጽ92) ስለ ድርብ ዓረፍተነገር (ገጽ114)፣ ስለውብስብ ዓረፍተነገር (ገጽ131)፣ ስለተውሳከግስ (ገጽ155) የቀረቡት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አደረጃጀት ስልት የተደራጁ ናቸው። ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ መጀመሪያ ስለያዙት ርእሰ ጉዳይ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ከሰጡ በኋላ ይህንኑ መሰረት ያደረጉ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያዛሉ፡በመሆኑም ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ገለጻዎቹንና ምሳሌዎችን ካጤኑ በኋላ መልመጃዎቹን ወደመስራት፣ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ወደመለማመድና ተግባራዊ ወደማድረግ ይሸጋገራሉ ማለት ነው። ለዚህም

አስረጅ ይሆነን ዘንድ የሚከተለውን ከመማሪያ መጽሀፉ የተወሰደ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ገለጻ እንመልከት፡፡

ማስታወሻ

አንድ ዓረፍተነገር ዓረፍተነገር ለመባል ቢያንስ ሁለት መዋቅሮችን የያዘ መሆን አለበት፡፡ እነሱም፡-

ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ናቸው፡፡ ባለቤት በዓረ
ፍተነገር መነሻ የሚገኝ ሲሆን፣ ማሰሪያ አንቀ
ጽ ደግሞ ዓረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ የሚገኝ
ነው፡፡ ምሳሌ፡- ከድር ከትምህርት ቤት መጣ፡፡
ከድር የዓረፍተነገሩ ባለቤት ሲሆን፣ መጣ
ደግሞ ማሰሪያ አንቀጽ ነው፡፡ /7ኛክፍል፣ገጽ9/

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጾችን ለይታችሁ ጻፉ

ሀ. ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

ለ. እንስራ ውሀ ይይዛል፡፡

ሐ. አበበና አለሙ ኳስ ተጫወቱ፡፡

ከቀረበው አስረጅ ስለዓረፍተ ነገር መዋቅሮች/ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ/ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ አቅርቧል፡፡ ከዚያም ከገለጻውና ምሳሌዎቹ ጋር ተዛመጅነት ያለው መልመጃ ቀርቧል፡፡ ይህም አቀራረብ ተማሪዎች አስቀድመው ሰዋስዋዊ ገለጻውንና ምሳሌዎቹን እንዲገነዘቡ፣ቀጥለው ደግሞ በተገነዘቡት መሰረት ተዛማጅ መልመጃዎችን ወደመስራት እንዲሸጋገሩ ደርጋቸዋል፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ብዛቹ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት ተደራጅተው መቅረብ መቻላቸውን ያመላክታል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ነው ወይስ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የትኛው አደረጃጀት በስፋት ይገኛል?" በሚል ለተጠየቁት ጥያቄ አንደኛው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት በስፋት ይገኛል፡፡ ማለትም ስለሚማሩት ሰዋስዋዊ ይዘት በቅድሚያ ገለጻ ይሰጣል፡፡ ከዚያም መልመጃ እንዲሰሩ ያዛል የሚል ሲሆን፣ የሁለተኛውም ምላሽ አብዛኛው የመጽሀፉ አደረጃጀት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

### ለ. የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ

በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ሁለት ብቻ እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነሱም ስለ ግስ ባህርያት (የኃላፊ፣የአሁን፣የትንቢት፣ገጽ41)፣ ስለነጠላ ዓረፍተነገርና ጥገኛ ሐረግ(ገጽ 55) የቀረቡት ናቸው፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መጽሀፉ ወስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እጅግ በጣም ትንሽ እንደሆኑ ሲሆን ብዙዎቹ ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልትን ተከትለው የተደራጁ እንደሆነ ከዚህ በፊት ባነሳነው ክፍል ተገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አንድ አይነት የአደረጃጀት ስልት ብቻ መከተል ትምህርቱን አሰልችና የሚጠላ ሊያደርገው ይችላልና የተለያዩ የአቀራረብና የአደረጃጀት ስልቶችን እንደሁኔታውና አስፈላጊነቱ አመጣጥኖ መጠቀም ተገቢ እንደሆነ በክለሳ ድርሳን አውስተናል፡፡ የሚከተለውን ከመጽሀፉ የተወሰደ ሰዋስዋዊ ገለጻ እንመልከት፡፡

ማስታወሻ

ባለቤት (ድርጊት ፈጻሚ) እና አንድ ማሰሪያ አንቀጽ ያለው የቃላት ስርዓታዊ ስብስብ ነጠላ ዓረፍተነገር ይባላል፡፡ የዓረፍነገሩ ግስ እንዳያስር ሙሉ ስሜት እንዳይሰጥ ሲደረግ ደረጃው ዝቅ ብሎ ጥገኛ ሐረግ ይሆናል፡፡ ምሳሌ፡- 1.ሰናይት እንጀራ ትጋግራለች፡፡

ሰናይት እንጀራ ስትጋግር

2.ማሩ ወደሰማይ ጦር ወረወረ፡፡

ማሩ ወደሰማይ ጦር ሲወረውር

/ስምንተኛ ክፍል፣ ገጽ 55/

1.የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ወደጥገኛ ሐረግ ለውጣችሁ ጻፉ

ሀ.ልጆች ወሰላጆቻቸውን ያከብራሉ፡፡

ለ.መላኩ በመኪና ወደ ጎጃም ሄደ፡፡

በአስረጅነት የቀረበውን ሰዋስዋዊ ይዘት ስንመለከት ይዞት ስለተነሳው ርእሰ ጉዳይ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ሰጥቷል፡፡ በማስከተልም ከማስታወሻው ጋር ተያያዥ የሆኑ ተማሪዎች የሚሰሯቸው መልመጃዎች ተዘጋጅተውላቸዋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት የተደራጁ ይዘቶች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡ ይሁን እንጂ በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ሁለት መምህራን "በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት ነው ወይስ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት የተደራጀው የትኛው በስፋት ይታያል"? በሚል ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህር "ሀ"፣ አብዛኛው የመጽሀፉ አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንደሆነ አልፎ አልፎ ደግሞ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የተደራጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሁለተኛው መላሽመምህር "ለ" አስተያየት መጽሀፉ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት በስፋት እንደሚታይ የሚገልጽ ነው፡፡

# ምእራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዓላማው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም. ስራ ላይ በዋሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶችን አቀራረብ እና አደረጃጀት መተንተን ነው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ የሰዋስው ይዘቶቹ አቀራረብ እና አደረጃጀት በክለሳ ድርሳን ከቀረቡት ንድፈ ሀሳቦች አንጻር ተተንትኗል። በሰነድ ፍተሻ እና ከመምህራን በተገኘ ቃለ-መጠይቅ ምላሽ መረጃዎች ጋር በማቀናጀት ትንተናውን ለማጠናከር ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በትንተናው ሂደት የሚከተሉትን ጥሩ ጎኖች እና ክፍተቶች ለማስተዋል ተችሏል።

**በትንተናው የታዩ ጥሩ ጎኖች**

- በሰባተኛና በ8ኛ ክፍል መጻህፍት የምሳሌዎች የግልጽነት ችግር አልታየም።
- ከትክለኛነት አንጻር የሁለቱም መጻህፍት በክፍተት ከታዩት በስተቀር ጥሩ ነው።
- የተገቢነት ችግር በሁለቱም መጻህፍት በትንተና ከተገለጸው ውጭ አልተገኘም።
- ከተከታታይነት አንጻር በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ከቀረቡት ሀያሰባት ይዘቶች አስራሁለቱ (44.4%) የሚሆኑት ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ ተደጋግመዋል።
- በ8ኛ ክፍል ከቀረቡ ሃያ አንድ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል 16ቱ (76%) በመማሪያ መጽሀፉ የተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመዋል።
- በሁለቱም መጻህፍት ከተካተቱ ሰላሳ አንድ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ውስጥ 17ቱ (54.8) በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ውስጥ ሳይቆራረጡ በተታታይነት ተገኝተዋል።

**በትንተናው የታዩ ክፍተቶች**

- በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ብዙ ጥቅል ሀሳቦችን የያዙና ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው ግልጽ ሀሳብ የማያስተላልፉ ትእዛዞች ታይተዋል፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎችና ማስታዎሻዎች ግልጽ ያለመሆን ችግር እንዳለ ተስተውሏል፡፡
- በሁለቱም መጻህፍት ከስነ-ድምጽ የሰዋስው ክፍል የቀረበ ይዘት አልታየም፡፡በሁለቱም መጻህፍት ከሶስቱ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ ይዘቶች ብቻ ቀርበዋል፡፡ ይሁንእንጂ እነዚህም በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ የተመጣጣኝነት /የሚዛናዊነት/ ችግር እንዳለ ታይቷል፡፡
- የይዘቶች ተከታታይነት ሁኔታ በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ አስራአምስት(55.5%) የሚሆኑት ይዘቶች አንድ ጊዜ ብቻ የተከሰቱ ናቸው፡፡ በተደጋገሙትም ይዘቶች መካከል ከፍተኛ የተመጣጣኝነት ችግር እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በሰባኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ በአብዛሀኛው የይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ የመሄድ ድክመት እንዳለ ተስተውሏል፡፡ በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ድክመት የታየባቸው በጣም ትንሽ ይዘቶች ተገኝተዋል፡፡
- በሁለቱ መጻህፍት ከቀረቡት በቁጥር አስራ አራ (45.1%) ያህሉ ተለጣጣቂነት የሌላቸው መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ሳይቆራረጡ የቀጠሉ ይዘቶች ላይ አልፎ አልፎ ስፋትና ትልቀት ጨምሮ ያለመገኘት ችግር ታይቷል፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልቶች እንደተከሰቱ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ተመጣጣኝ ሆነው አልቀረቡም፡፡ ማለትም ሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት በስፋት ሲታይ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት ደግሞ በጣም ጠቂት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ በስምንተኛ ክፍል ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት በስፋት ይታያል፤ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልት የቀረቡ ሁለት ይዘቶች ብቻ ተገኝተዋል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት የታዩ ጠንካራ ጎኖች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የአጥኛዋ አስተያየት ነው፡፡

መጽሃፍ ዝግጅጽ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያልቅ ባለመሆኑ የመማሪያ መጻህፍቱ እንደገና ሲዘጋጁም ወይም ሲሻሻሉ በሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት የታዩ ድክቶች እርምት ሊደረግባቸው ይገባልና የሚከተሉትን መፍትሄ ሀሳቦች ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

- የሰዋስው ይዘት ትእዛዞች፣ምሳሌዎች፣ጥያቄዎችና ማስታወሻዎች ላይ የታዩ የግልጽነት ችግሮች በተቻለ መጠን ማስተካከል ቢቻል፣
- በመማሪያ መጻህፍቱ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከሁሉም የሰዋስው ክፍሎች የተውጣጡ ቢሆንና ተመጣጣኝነት ቢኖራቸው፣
- በመጽሀፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሁሉም ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተቻለ መጠን ተደጋግመው ቢቀርቡ፣ መደገም ብቻ ሳይሆን ስፋትና ትልቀታቸው ከምእራፍ መእራፍ እየጨመረ እንዲሄድ ቢደረግና ድግግሞሹ እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ ቢሆን፣ አሰልች የይዘት ድግግሞሽ ቢወገድ፣
- በመመማሪያ መጻህፍ የተካተቱ ሁሉም የሰዋስው ይዘቶች ቀጣዪነት ኖሯቸው ቢቀርቡ፣ ስፋስትና ጥልቀታቸውም እየተሸሻለ እንዲሄድ ቢደረግ፣
- ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልቶች ተመጣጣኝ ሆነው ቢቀርቡ፣
- ለክፍል ደረጃዎቹ ተማሪዎች ተገቢ ያልሆኑና በቂ ያልሆነ ማብራሪያ የማይሰጡ ማስታዎሻዎች እንዳይኖሩ ጥረት ቢደረግ፣
- ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና እና ከአተቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቶች እንደ አስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ ቢሆኑ፣

## ዋቢ ጽሁፎች


ሁሉባንተ አደመ (1994) "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስተየተዘጋጁ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ መሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ። አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ(ያልታተመ)።

ሐዋዝ ወልደየስ (2000) "በአዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማራኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንጽጽራዊ ጥናት::" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ትናታዊጽኁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ሰሚራ አሊ (2010) "በደቡብ ክልል ስራ ላይ በበዋለው የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ።" የሁለተኛ ዲግሪማሟያጥናታዊ ጽሁፍ።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ባየ ይማም።(1987)። *የአማርኛ ሰዋስው፡*አዲስ አበባ ፣ት.መ.ማ.ማ.ድ።

ባዩ ተሾመ (2004) "በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መመሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጀጀት ግምገማ።" የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ኒቨርሲቲ(ያልታ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር።(2004)።*አማርኛ የተማሪ መጽሀፍ አስረኛ ክፍል፡*ዱባይ ፣ የአል-ጉሬር አሳታሚ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። (2011)። *የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ የተሻሻለ ሁለተኛ እትም*: አዲስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ቢ.ኢ. ማተሚያ ቤት።

Allwht, R.L. (1981) "What Do We want Teaching Materials For" ELT Journal Vol. 36. No.1,5–18.

Batstone, R. (1994). *Grammar*. Oxford: Oxford University Press.

Brown ,D. (1994). *Principle of Language Learning and Teaching*.USA: Prentice Hall.

Bygate,M.,Tonkyn,A. and Wlliams,E. (1994). *Grammar and the Language Teacher*. (eds) London: Prentice Hall International.

Brown, D. (1994). *Prenciples of Languge and Teaching Practice* Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Cross, D. (91991). *A Practical H and book of Language Teaching.* London: Cassel Villiers House.

Cnningsworth, A.(1995). *Choosing Your Course Book*.Oxford: Heineman.

Donough, J. and Show (1995).*Material and Methods in ELT.Ateachers Guides*. Oxford: Blanck Well.

Dubin and Olshatain, E. (1986).*Cours Design*: Cambridge. Cambrige University Press.

Edge,J. (1993). *Essentials of English Language Teaching.* London: longman.

Grant, N. (1987). *Makinge the Most of Your textbooks*. London: Longman.

Greenbaun, S. (1998). Referance Grammars and Pedagogical Grammars; World Englishes,Vol. 6, no. 3,191 - 7.

Harmer, J. (1987).*Teaching and Learning Grammar*.London: Longman.

Larsen-Freeman,D. (1986). *Techniques and Principles in Language Teaching*.Oxford: Oxford University Press.

------------. (1991). *Teaching Grammar*. In Celce-Murcia, M.*Teaching English as second or foreign Language*. Boston: Heinman publisher. Pp 246-295.

Leech, G. (1994). ″Students Grammar Teachers Grammar-Learners Grammar″ in Bygate, M Tonkyn, A. and Williams, E.(ed). Grammar and theLaguageTeacher : New york Prentice Hall.

Nunan, D.(1988). *Syllabus Design*.Oxford:Oxford University Press.

Richards, J. and Rodgers, T. (1986).*Approaches and Methods in Language Teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Sheldon , L.E. (1988). "Evaluating ELT Text Book and Materials."ELT Journal.Vol.42, No 4,237 - 246.

Stern, H.H. (1983). *Fundamental Concepts of Language Teaching*.Oxford: Oxford University Press.

-------- (1992).*Issuse and Options in Language Teaching*.Oxford:Oxford University Press.

Stevick, E.W. (1986).*Images and Options in The Language Classroom.*Cambridge: Oxford Uiversity Press.

Swan, M. (1994). "Design Criteria for Pedagogical Language Rules."In Bygate, M. 'tal'(eds.), Grammar and the Language Teacher. (pp. 45- 55). New York: Printice Hall.

Taba, H.(1962). *Curriculum Development Theory and Practice*. New York. Harcourt Brace Jovanovich.

Tonkyn, A. (1994). "Introduction: Grammar and the Language Teacher."In Bygate,M et al. .(eds), Grammar and the Language. ( PP.1-14). NewYork: Printice Hall.

Tyler, R.W.(1949). *Basic Prenciples of Curriculum and Introduction*. Chicago.The University of Chicago Press.

Ur, P. (1994). *A cours in Languge Teaching: Practice and Theory*. Cambredge: Cambredge University Press.

**አባሪዎች**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ**

**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ-ምረቃ መርሃግብር**

**ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚቀርብ ቃለ-መጠይቅ**

**መምህር ሀ፡-**

1.የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም--------ሮቢት አንደኛ ደረጃ

2. ጾታ--------------------ወ

3. የትምህርት ደረጃ------ዲግሪ

4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ----አማርኛ መምህርነት፣ሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ---8ኛ

5. የአገልግሎት ዘመን----------18 ዓመት(አከለ

*ቃለ-መጠይቁ ተደረገበት ቀን-------23/10/2015ዓ.ም*

**መምህር ለ፡-**

1 .የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም---------ጎብዬ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ

2. ጾታ------ሴ

3. የትምህርት ደረጃ-----------ዲግሪ

4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ------------አማርኛ፣ የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ----8ኛ

5. የአገልግሎት ዘመን-----------10 ዓመት

*ቃለ-መጠይቅ የተደረገበት ቀን-------22/10/2015ዓ.ም*

**መምህር ሐ፡-**

1.የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም----------ሮቢት አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ

2. ጾታ--------------ወ

3. የትምህርት ደረጃ---------ዲግሪ

4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ዐቢይ--- አማርኛ፣ የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ-- 7ኛ

5. የአገልግሎት ዘመን-----------35 ዓመት

ቃለ-መጠይቁ ተደረገበት ቀን---22/10/2015ዓ.ም

**መምህር መ፡-**

1.የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም------------ሮቢት አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ

2. ጾታ----------ወ

3. የትምህርት ደረጃ----------ዲፕሎማ

4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ-----------አማርኛ፣ የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ --7ኛ

5. የአገልግሎት ዘመን--------------------8 ዓመት

ቃለ-መጠይቁ ተደረገበት ቀን------23/10/2015ዓ.ም

**በመጻህፍቱ ውስጥ የሰዋሰው ይዘቶችን አቀራረብ የሚመለከቱ ጥያቄዎች**

**ጥያቄ** 1፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋሰዋዊ ገለጻዎች /ማስታወሻዎች፣ምሳሌዎችና ጥያቄዎች ለተማሪዎች ምንያህል ግልጽሆነው ቀርበዋል ይላሉ?

መልስ፡-

<u>መምህር ሀ</u>. ሰዋሰዋዊ ማስታወሻዎች፣ምሳሌዎችና ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ግልጽ ናቸው፡፡አልፎአልፎ ግን ተማሪዎች ምን ማለት ነው ብለው የሚጠይቋቸው ግልጽ ያልሆኑ አሉ፡፡

<u>መምህር ለ</u>. ማስታወሻዎቹ ላይየግልጽነት ችግር አለ፤ማለትም የሚቀርቡት ማብራሪያዎችና ገለጻዎች በቂአይደሉም

መምህር ሐ. ዋሰዋዊ ገለጻዎች፣ምሳሌዎችና ጥያቄዎች ግልጽናቸው፡፡ወደፊት ስለሚማሩት ህግ ግንዛቤ የሚፈጥሩ፣ስለሚሰሯቸው መልመጃዎች ፍንጭ የሚሰጡ ናቸው፡፡

መምህር መ. ብዙዎቹ የሰዋሰው ገለጻዎችና፣ምሳሌዎ፣ ጥያቄዎች ግልጽናቸው፡፡

**ጥያቄ** 2. በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋሰው መልመጃ ትእዛዞች ምንያህል ግልጽ ናቸው?

መልስ፡-

መምህር ሀ. የመልመጃ ትእዛዞ በአብዛኛው ግልጽ ናቸው፡፡ አንዳንድ ተማሪዎ እንዴት ነው የምንሰራው ብለው የሚጠይቋቸው ግልጽነት የሌላቸው አሉ፡፡

መምህር ለ. እኔ ትእዛዞቹ ላይ ችግር አላየሁም

---

መምህር ሐ.የመልመጃ ትእዛዞች አጠር ያሉና ግልጽ ናቸው፡፡

መምህር መ. አብዛኛዎቹ ትእዛዞች ድፍን ያሉና ግልጽ ያልሆኑ ናቸው፡፡ መምህሩ ያብራሩላችሁ የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህም ተማሪዎች በራሳቸው ለመገንዘብ ይቸገራሉ፡፡

**ጥያቄ.** 3. በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ልዩልዩ ሰዋሰዋዊ ክፍሎች በተመጣጠነ ሁኔታ ከማካተት አንጻር ምን ገጽታ አላቸው ይላሉ?

መልስ፡-

መምህር ሀ. የሰዋስው ትምህርት ክፍሎችን መመጣጠን በሚመለከት የተመጣጠነ አይደለም፡፡ ስነድምጽ የለም፡፡ በብዛት ያለው አውዳዊ ፍች ነው፡፡

መምህር ለ. የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ከሁሉም ክፍል የተመጣጠኑ ዐይደለም፡፡ ለምሳሌ ከጥያቄው ማብራሪያ እንደተረዳሁት ስነድምጽ በጭራሽ የለም፡፡ በብዛት አውዳዊ ፍች አለ፡፡

መምህር ሐ.ከሁሉም የሰዋስው ትምህርት ክፍል የተውጣጡ ናቸው፡፡ አውዳዊ ፍች ግን ይበዛል

መምህር መ.የተካተቱት የሰዋው ይዘቶች የተመጣጠኑ አይደሉም፡፡ ሁሉንም ሰዋሰው ክፍሎች አያካትትም፡፡ ለምሳሌ ስነድምጽን የተመለከተ የተካተተ ይዘት ለም፡፡ ቃላት ፍች ብዙ ይደጋገማል፡፡

**ጥያቄ** 4፡- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰዋሰውን ለማስተማር የተካተቱ ይዘቶች ከደረጃ ተማሪዎች የመስራት አቅምና/ተገቢነት/ ተገቢውን እውቀት ከማስጨበጥ አንጻር እንዴት ይገልጿቸዋል?

መልስ፡-

<u>መምህር ሀ</u>. በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ከተማሪዎች የመስራት አቅም በላይ አይደሉም፡፡ እንዲያውም ያነሰ ነው፡፡ ተማሪዎች ይህ ቀላል ነው ሌላ እንማር ይላሉ፡፡

<u>መምህር ለ</u>. የሰዋሰው ይዘቶቹ ከደረጃው ተማሪዎች የመስራት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡

<u>መምህር ሐ</u>. እኔ ከተማሪዎች የመስራት አቅምና ተገቢውን እውቀት ከማስጨበጥ አንጻር ተመጣጣኝ ናቸው ነው የምለው፡፡

<u>መምህር መ</u>.የተካተቱት ይዘቶች ከተማሪዎች የመስራት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ እንዲያውም ያንሳል /በቂ አይደለም ባይ ነኝ፡፡

**ጥያቄ** 5. በመማሪያ መጽሀፎቹ ውስጥየተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ትክክለኛ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ከማሳየት አኳያ ምን ገጽታ አላቸው?

መልስ፡-

<u>መምህር ሀ</u>. በስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ይዘቶች ትክክለኛውን ስርዓት የተከተሉ ናቸው፡፡ ስህተት አላየሁም፡፡

---

<u>መምህር ለ</u>. በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ስህተት የሆነ ሰዋስው ይዘት የለም፤ ትክክለኛውን የቋንቋ ስርዓት የተከተለ ነው፡፡

<u>መምህር ሐ</u>. በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች ትክክለኛ የሰዋሰው ስርዓት የተከተሉ ናቸው፤ ስህተት የሆነ ለም፡፡

<u>መምህር መ</u>. ስህተት የሆነ ሰዋስው ይዘት በመጽሀፉ ውስጥ አላየሁም፡፡ሰ

**በመጻህፍቱ ውስጥ የሰዋሰው ይዘቶችን አደረጃጀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች**

**ጥያቄ** 6. ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ ከተከታታይነት አንጻር ማለትም በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው ከመቅረብ አንጻር ምን አይነት ገጽታ አላቸው?

መልስ፡-

መምህር ሀ. በአብዛኛው ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩምእራፎች ሲከታተሉ አይታይም/ድግግሞሽ የላቸውም፡፡

መምህር ለ.ይዘቶቹ በተለያየ ምእራፍ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡አንዳንድ የማይደጋገሙም አሉ፡፡

መምህር ሐ. ይዘቶች አልፎ አልፎ ተከታታይነት ባለው መልኩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

መምህር መ. ተከታታይነትን በሚመለከት ብዙ ይዘቶች ተደጋግመው ይመጣሉ፡፡

**ጥያቄ** 7. በመማሪያ መጽሀፎቹ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሄዱ ናቸው፤ወይስ ለውጥ አይታይባቸውም?

መልስ፡-

መምህር ሀ. ከላይ እንደገለጽኩት የይዘት ድግግሞሹ አናሳ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ጥልቀቱንም ማየት አይቻልም፡፡ አንዳንድ የተደጋገሙ ይዘቶችንም ስናይ ጥልቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ አይይም፡፡

መምህር ለ. የይዘት ድግግሞሹ ቢኖርም ጥልቀቱ እየጨመረ ሲሄድ አይታየኝም፡፡

መምህር ሐ. የሚደጋገሙ ይዘቶች እንደ አቅማቸው ሰፋ ብሎና ጥልቀቱ ጨምሮ ነው የተደጋገሙት፡፡

መምህር መ. በመጽሀፉ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አልፎ አልፎ ስፋትና ጥልቀታቸው እጨመረ የሚሄድ አሉ፡፡ አብዛኛው ግን ምንም ቅርጽ ሳይቀየር አሰልች የሆነ የመልመጃ ድግግሞሽ ይታያል፡፡

**ጥያቄ** 8. በመማሪያ መጽሀፎቹ ውስጥ የሚገኙ የሰዋሰው ይዘቶች የደረጃው ተማሪዎች ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ናቸው?

መልስ፡-

<u>መምህር ሀ</u>. ሰዋስዋዊ ይዘቶች ሙሉበሙሉ ባይሆንም በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ይዘቶች ከዚህ በፊት በነበሩ ክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ወይም ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡

<u>መምህር ለ</u>. በክፍል ደረጃው መጽሀፍ የተካተቱ ይዘቶች ከዚህ በፊት ባሉ የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው መሆኑን ተማሪዎች ጡሙናል፡፡ መጽሀፉ አዲስ ነው፡፡

<u>መምህር ሐ</u>. እኔ እንደሚመስለኝ  በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ተማሪዎች ከዚህ በፊት ባሉ የክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ነቸው፡፡

<u>መምህር መ.</u>በእኔ እምነት አብዛኛዎቹ የሰዋስው ይዘቶች ተማሪዎች ቀደም ባሉት ክፍል ደረጃዎች የተማሯቸው ናቸው፡፡

**ጥያቄ 9**. በመማሪያ መጽሀፎቹ ውስጥ የተካተቱ ሰዋሰዋዊ መልመጃዎች የተደራጁት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ነው፤(በቅድሚያ ስለሚማሩት የቋንቋ ህግጋት ሊጠቀሙ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ) ወይስ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር(በቅድሚያ ስለሚማሩት የቋንቋ ህግጋት ገለጻ ለተማሪዎች ይቀርባል) ነው? የትኛው አደረጃጀት በስፋት ይገኛል?

መልስ

<u>መምህር ሀ</u>. የሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ አብዛኛው አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አተቃላይ ነው፡፡ አልፎአልፎ ደግሞ ከአተቃላይ ወደ ዝርዝርም ነው፡፡ ማለትም መልመጃ ተማሪዎች ከመስራታቸው በፊት ማስታወሻ/ገለጻ ይሰጥና በማስታወሻው መሰረት ጥያቄዎችን ስሩ ይላል፡፡

<u>መምህር ለ.</u> እኔ እንዳየሁት መጽሀፉ ውሰጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃት በስፋት ይታይበታል፡፡

<u>መምህር ሐ.</u> በሰባተኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ሁለቱም አደረጃጀቶች ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት በስፋት ይገኛል፡፡ በመጀመሪያ ስለሚማሩት ህግ ገለጻ ያቀርባል ከዚያም ወደ ተግባሩ ይሄዳል፡፡

<u>መምህር መ.</u> አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት የተደራጁ ናቸው፡፡ የተወሰኑ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የተደራጁ አሉ፡፡

**ማረጋገጫ**

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሙኒኬሽን የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር የሰዋው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና (በአማራ ክልል በ2015 ዓ.ም. ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መጻህፍት ተተኳሪነት) በሚል ርእስ ለማስተርስ (MA) ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው።

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማየን ያስቀመጥኩኝ የድህረ-ምረቃ ተናሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሁፎች ምንጫቸውን በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

1. ስም- ሙሉ ደርቤ
2. ፊርማ-----------------------
3. አድራሻ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ